# መቅድም

አንድ ቋንቋ የአንድ ብሔረሰብ ማንነት መገለጫ ከሆኑት እሴቶች መካከል ዋንኛው ብቻ ሳይሆን፣ የባህል፣ የአስተሳሰብና የእውቀት መገለጫና መከማቻም ጭምር ነው፡፡ የአንድ ቋንቋ መጥፋት ላንድ ብሔረሰብ ልዩ የሆኑ እሴቶች መጥፋትም ነው፡፡ ስለዚህም ቋንቋዎች እንዳይጠፉ መጣር፣ መጥፋታቸውን ማዳን የማይቻል ከሆነ ደግሞ የቋንቋዎቹን ሁለንተና ቢቻል ከነባህላዊ እሴቶቻቸው መዝግቦ ማቆየት ጠቃሚ ነው፡፡

አርጎብኛ በመጥፋት ላይ የሚገኝ ቋንቋ ነው ቢባልም መንሰራራት የሚችልበት ደረጃ ላይ እንደሆነ በቅርቡ ኤስ.አይ.ኤል ኢትዮጵያ በተባለ አለም አቀፍ ግብረ ሰናይ ድርጅት ጥናት ተመልክቷል (Hussen et al 2006).

ይህንኑ ከግንዛቤ በማስገባት የአርጎባ ልማት ማህበር የአርጎብኛ ቋንቋ ጨርሶ ሳይጠፋ ቢያንስ ለብሔረሰቡ ተወላጆች ቋንቋውን ለማስተማር የሚያስችል ዝግጅት አድርጎ ፕሮጀክቶች በመንደፍ እየተንቀሳቀሰ ይገኛል፡፡ ከነዚህም መካከል የማስተማሪያ መፅሀፍ፣ የመዝገበ ቃላት እና የሰዋሰው መጽሀፍ ዝግጅቶች ይገኙበታል፡፡ ይህ የማስተማሪያ መፅሀፍ የልማት ማህበሩ እቅድ ነድፎ እያከናወነ ካላቸው ፕሮጀክቶች ውስጥ አንዱ መሆኑ ነው፡፡ አርጎብኛ በውል የተለዩ ሁለት አይነት ዘዬዎች አሉት፡፡ እነዚህ ዘዬዎች በወሎ፣ በሸንኬና ጦልሀ አካባቢ የሚነገረው **የሸንኬ-ጦልሀ ዘዬ** እና በአልዩ አምባና በአቅራቢያው የሚነገረው፣ **የአልዩ አምባ ዘዬ** በመባል የሚታወቁት ናቸው፡፡ በነዚህ ዘዬዎች መሀከል ያለው ልዩነት ተጨማሪ ጥናት የሚያስፈልገው ቢሆንም ሰፊ መሆኑን የኤስ. አይ. ኤስ ሪፖርት ያሳያል፡፡ ይኸው ሪፖርት ሁለቱን ባንድ እያጣመሩ ለማስተማሪያነት ማዘጋጀቱን ለጊዜው ወደጎን በመተው በእያንዳንዳቸው ላይ እራሱን የቻለ የማስተማሪያ ዝግጅት እንዲደረግ ከላይ የቀረበ ነው፡፡ ይህ የማስተማሪያ መፅሀፍ የተዘጋጀው የአልዩ አምባውን ዘዬ መሰረት በማድረግ ነው፡፡ በቀጣይ ይህንኑ አይነት መፅሀፍ በሸንኬ ጦልሀው ዘዬ ለማዘጋጀት በመቀጠልም ሁለት ዘዬዎች ልዩነታቸው ጠባብ ሆኖ

አንድ መደበኛ ዘዬ ማዳበር የሚቻል ከሆነ በዚያው መልክ የዘዬ አይነት መፅሀፍ ለማዘጋጀት ሃሳብ አለን። ለዚህ መፅሀፍ ዝግጅት ስኬት የበኩላቸውን አስተዋፅኦ ያደረጉልንን ሁሉ ከልብ እናመሰግናለን። በተለይ አቶ ሰይድ ኡመር የአርጎባ ልማት ማህበር ስራ አስኪያጅን ከልብ ልናመሰግናቸው እንወዳለን።

# 1. መግቢያ

የራሳቸዉ ቋንቋ ካላቸዉ የሀገራችን ህዝቦች መካከል አንዱ የአርጎባ ህዝብ ሲሆ ቋንቋዉ አርጎብኛ በመባል ይታወቃል ።

በኢትዮጲያ ቋንቋዎች ስርጭት በቤተሰብ አመዳደብ አርጎብኛ የሴም ቋንቋ አካል ነዉ። ሴማዊ የቋንቋ ቤተሰብ በምእራብና በምስራቅ ለሁለት የተከፈለ ሲሆን የምዕራቡ ክፍል እንደገና በመሀል ሴማዊና በደቡብ ሴማዊ የተከፈለ ነዉ ። ደቡብ ሴማዊ በተራዉ በደቡብ ዓረቢያ ቋንቋዎችና በኢትዮ ሴማዊ ይከፈላል ። የኢትዮ ሴማዊ የቋንቋ ቤተሰብ በኢትዮጲያ የሚገኝ ሲሆን ይህ የቋንቋ ቤተሰብ በኢትዮጲያ ዉስጥ በሁለት ክፍል ይመደባል ። ይሄዉም ደቡብ ኢትዮ ሴማዊና ሰሜን ኢትዮ ሴማዊ በመባል ሲሆን ሰሜን ኢትዮ ሴማዊ ግዕዝ ፣ ትግረንና ትግሪኛን ደቡብ ኢትዮ ሴማዊ የቋንቋ ወገን ደግሞ አማርኛ ፣ጉራጊኛ ፣ አርጎብኛ ፣ አደሬኛና ጋፋትን ይዞ የሚገኝ ነዉ ።

በሌላ የመረጃ ምንጭ የአርጎብኛ ቋንቋ ቤተሰብ አመዳደብ በኢትዮጵያ የሴማዊ ቋንቋ ቤተሰብ (Ethio-Semetic Language Family ) ዉስጥ በደቡባዊ የኢትዮ- ሴማዊ ቋንቋዎች (South Ethio-Semetic Language ) የሚመደብ መሆኑን እንደዚሁም ይህ አመዳደብ መልክአ ምድራዊ ብቻ ሳይሆን ስነ-ልሳናዊ መሠረት አንዳለዉ በሰነድ ተመዝግቧል ።

የአርጎብኛና የአማርኛ ቅርርብ ከዘዬ ያለፈ ቢሆንም በቃላት፣ በሰዋሰው ወዘተ ያላቸው ዝምድና ከፍተኛ ነው። እነዚህ ቋንቋዎች ከማናቸውም ሌላ ቋንቋ ጋር ካላቸው ቀረቤታ ይልቅ እርስ በእርሳቸው ይቀራረባሉ። ስለዚህም በዚህ የማስተማሪያ መፅሀፍ አጠቃቀሞችን በተመለከተ የቀረበው ማብራሪያ እጅግ

የተመጠነ ነው። መፅሀፉ አርጎብኛን ምንም ለማይችሉ ሰዎች የተዘጋጀ ነው። አላማው ቋንቋውን የማይናገሩ የብሄረሰቡ አባላት (እና ሌሎች ፍላጎት ያላቸው) እንዲማሩት የመነሻ መፅሀፍ ሆኖ እንዲያገለግል የተዘጋጀ ነው። በቋንቋው ብቁ ተናጋሪ ለመሆን ይህ መፅሀፍ ብቻ በቂ ነው ብለን አናስብም። በዚህም ምክንያት ቋንቋውን በመጠነኛ ደረጃ ለሚችሉ ሰዎች የሚያግዙ እንደደረጃቸው ቀጣይ መፅሀፍትን ለማዘጋጀት እቅድ አለን።

ይህ መፅሀፍ ሰባት አበይት ክፍሎች አሉት። የመጀመሪያው የአርጎብኛን ፊደልና አፃፃፍን የሚያስተምር ነው። ሁለተኛው ክፍል የሰላምታ ልውውጥን ያስተምራል። ሶስተኛው ...

# ክፍል አንድ፡ የአርጎብኛ ፊደል ገበታና አፃፃፍ

ለአንድ ቋንቋ በፅሁፍ መዳበር ተቀዳሚ ተግባር ወጥ የሆነ አፃፃፍ መኖር ስለሆነ እዚህ የተጠቀምንበት አፃፃፍ የአርጎባ ልማት ማህበር በባለሙያ አስጠንቶ በ1999ዓ.ም ያቀረበውን ነው፡፡ ይህ አፃፃፍን በአግባቡ ለመጠቀም ከአርጎብኛ ስነድምፅ ባህርይ አንፃር ሰፋ ያለ ትንታኔ መስጠት አስፈላጊ መስሎ ስለታየን ይህንኑ አድርገናል፡፡

## የአርጎብኛ ንጥረ-ድምፆችና የፊደሎች ውክልና

አርጎብኛ 24 ተነባቢ እና 7 አናባቢ ንጥረ-ድምፆች (phoneme) አሉት (cf. Leslau 1997)፡፡ እነዚህ ንጥረ ድምፆችን ቀጥለን እንመለከታለን፡፡ ንጥረ ድምፆቹ የተወከሉት ላቲንን መሰረት ባደረገ ስነድምፃዊ አፃፃፍ ነው፡፡

### *የአርጎብኛ ተናባቢ ንጥረ-ድምፆች*

ሰንጠረዥ 1፡ የአርጎብኛ ተናባቢ ንጥረ-ድምፆች

| ባህርየ-ፍጥረት | መከነ-ፍጥረት | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|---|
| | ከናፍራዊ | ከናፍር ወስናዊ | ድድ | ላንቃ | ትናጋ | ጉሮሮ |
| እግድ | b | | d | | g | |
| | | | t | | k | ʔ |
| | | | t’ | | k’ | |
| ተሹለክላኪ | | | z | ž | | |
| | | f | s | š | | h |

| | | | |
|---|---|---|---|
| ጓትግ | | | j |
| | | | c |
| | | | c’ |
| ሰርናዊ | m | n | ñ |
| ጎናዊ | | l | |
| ተርገብጋቢ | | r | |
| ከፊል-አናባቢ | w | | y |

የአርጎብኛ ተነባቢ ንጥረ-ድምፆች ከላይ በሰንጠረዥ 1 ላይ እንደምንመለከተው በቁጥር 24 ናቸው፡፡ እነዚህ ድምፆች ንጥረ ድምጽ ያስባላቸው ስርጭታቸው ሰፊ መሆኑና እያንዳንዳቸው ትርጉም ለዋጭ በመሆናቸው ነው፡፡ የአርጎብኛ የተነባቢዎች ሰንጠረዥ ከአማርኛው ጋር ሲነፃፀር የተወሰነ ልዩነት ያሳያል፡፡ ይህም ልዩነት አርጎብኛው ከአማርኛው የተለየ አንዳንድ ድምጾችን ይዞ መገኘቱ ነው፡፡ ወደ አናባቢ ንጥረ ድምጾች ከመምጣታችን በፊት ከላይ ያቀረብናቸውን የአርጎብኛ ንጥረ ድምፆች በኢትዮጵያዊ ፊደል ያላቸውን ውክልና ግዕዙን፣ ማለትም አንደኛውን ረድፍ ምልክቶች ወስደን እናሳያለን፡፡

| | | | |
|---|---|---|---|
| b | በ | f | ፈ |
| t | ተ | H | ኸ |
| š | ሸ | h | ሀ |
| s | ሰ | j | ጀ |
| d | ደ | c | ቸ |
| g | ገ | c’ | ጨ |
| k | ከ | m | መ |
| ? | ዐ | n | ነ |
| t’ | ጠ | ñ | ኘ |
| k’ | ቀ | l | ለ |
| z | ዘ | r | ረ |

w ወ y የ

## *የአርኅብኛ አናባቢ ንጥረ-ድምጾች*

ከላይ ለመግለፅ እንደሞከርነው የአርጎብኛ ንጥረ ድምፆች በቁጥር ሰባት ናቸው፡፡ እንኚዚህን አናባቢዎች በሚከተለው ሰንጠረዥ እናሳያለን፡፡

ሰንጠረዥ 2፡ የአርጎብኛ አናባቢ ንጥረ-ድምጾች

| | **የፊት** | **የመሀከል** | **የኋላ** |
|---|---|---|---|
| **የላይ** | i | ï | u |
| **የመሀል** | e | ä | o |
| **የታች** | | a | |

እነዚህ አናባቢዎች በኢትዮጵያዊው ፊደል፣ በተለይም በአማርኛው ውክልናቸው የሚከተለውን ይመስላል፡፡

i ኢ

e ኤ

ï እ

ä □

a አ/ኣ

u ኡ

o ኦ

ከላይ እንደምንመለከተው ሁለት ኢትዮጵያዊ ምልክቶች ማለትም /አ/ እና /ኣ/ አንድ ዓይነት ድምጽን /a/ ይወክላሉ፡፡ ይህ ከስነ ትምህርትም ሆነ ከሌሎቹ በርካታ መስፈርቶች አንጻር የማይደገፍ ነው፡፡ ስለዚህም በአርጎብኛው ፊደል ገበታ ላይ ይህ ድግግሞሽ ቀርቷል፡፡ በአርጎብኛው  ፊደል ገበታ /ኧ/ የሚለውን በመደበኛው በአማርኛው ፊደል ገበታ ዝርዝር የማይገኘውን በማስወገድ በፊደል ገበታው በአንደኛው እረድፍ የሚገኘው "አ"ንንበቱ ኧ /ä/ እንዲሆን ተደርጎ በአርጎብኛው ተወስዷል፡፡ በአርጎብኛው ፊደል ገበታ ያሉት አናባቢዎች ንበታቸው በቀላሉ ለመለየት እንዲያስችለን አፈጣጠራቸውን በሚያሳየው ሰንጠረዥ እናመለክታለን፡፡

ሰንጠረዥ ሶስት፡ የአርጎብኛ አናባቢ ንጥረ-ድምጾች የአርጎብኛ ፊደል ውክልና

| | የፊት | የመሀከል | የኋላ |
|---|---|---|---|
| የላ | ኢ | እ | ኡ |
| የመ | ኤ | አ | ኦ |
| የታች | | ኣ | |

ሰንጠረዥ 2ን ከሰንጠረዥ 3 ጋር በንጽጽር ስንመለከተው፣ ላቲኑን ፊደል መሰረት በማድረግ የቀረቡት የአርጎብኛ አናባቢ ንጥረ ድምጾች በአርጎብኛው ፊደል ያላቸው ውክልና የሚከተለውን ይመስላል፡፡

i ኢ

e ኤ

ï እ

ä አ

a ኣ

u ኡ

o ኦ

ይህ የአርጎብኛ ፊደል ከላይ ለመግለጽ እንደሞከርነው ከአማርኛው ጋር መጠነኛ ልዩነት አለው። አንደኛው ልዩነት ኧ የሚል ምልክት በአርጎብኛ አለመኖሩ ነው። ሁለተኛው አንድ ድምጽን በአማርኛ የሚወክሉት አ እና ኣ በአርጎብኛ ራሳቸውን የቻሉ የድምፅ ውክልና እንዲኖራቸው መደረጉ ነው።

## *የአርጎብኛ ፊደል ገበታ*

## ሰንጠረዥ 4: የአርጎብኛ ፊደል ገበታ

| | | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|---|
| ሀ | ሁ | ሂ | ሃ | ሄ | ህ | ሆ |
| ለ | ሉ | ሊ | ላ | ሌ | ል | ሎ |
| መ | ሙ | ሚ | ማ | ሜ | ም | ሞ |
| ረ | ሩ | ሪ | ራ | ሬ | ር | ሮ |
| ሰ | ሱ | ሲ | ሳ | ሴ | ስ | ሶ |
| ሸ | ሹ | ሺ | ሻ | ሼ | ሽ | ሾ |
| ቀ | ቁ | ቂ | ቃ | ቄ | ቅ | ቆ |
| በ | ቡ | ቢ | ባ | ቤ | ብ | ቦ |
| ተ | ቱ | ቲ | ታ | ቴ | ት | ቶ |
| ቸ | ቹ | ቺ | ቻ | ቼ | ች | ቾ |
| ነ | ኑ | ኒ | ና | ኔ | ን | ኖ |
| ኘ | ኙ | ኚ | ኛ | ኜ | ኝ | ኞ |
| አ | ኡ | ኢ | ኣ | ኤ | እ | ኦ |
| ከ | ኩ | ኪ | ካ | ኬ | ክ | ኮ |
| ኸ | ኹ | ኺ | ኻ | ኼ | ኽ | ኾ |
| ወ | ዉ | ዊ | ዋ | ዌ | ው | ዎ |
| ዐ | ዑ | ዒ | ዓ | ዔ | ዕ | ዖ |
| ዘ | ዙ | ዚ | ዛ | ዜ | ዝ | ዞ |
| ዠ | ዡ | ዢ | ዣ | ዤ | ዥ | ዦ |

| | | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|---|
| የ | ዩ | ዪ | ያ | ዬ | ይ | ዮ |
| ደ | ዱ | ዲ | ዳ | ዴ | ድ | ዶ |
| ጀ | ጁ | ጂ | ጃ | ጄ | ጅ | ጆ |
| ገ | ጉ | ጊ | ጋ | ጌ | ግ | ጎ |
| ጠ | ጡ | ጢ | ጣ | ጤ | ጥ | ጦ |
| ጨ | ጩ | ጪ | ጫ | ጬ | ጭ | ጮ |
| ፈ | ፉ | ፊ | ፋ | ፌ | ፍ | ፎ |
| ፐ | ፑ | ፒ | ፓ | ፔ | ፕ | ፖ |

## አፃፃፍ

### *«የዲቃላ» (ከናፍራዊ) ድምጾች አፃፃፍ*

አርጎብኛ እንደ አማርኛ "ኋ"፣ ኳን የመሳሰሉ ድምጾች አሉት። ሆኖም በሰንጠረዡ ላይ እንደምንመለከተው በአርጎብኛ ፊደል ገበታ ላይ እነዚህ ድምፆች የፊደል ውክልና የላቸውም። እንዚህ ድምጾች የሚፃፉት ለምሳሌ "ኳ" ን ክዋ፣ "ኋን" ግዋ በማድረግ ነው። ለዝርዝር ምክንያቱ የፊደል ገበታውን ለመቅረፅ የተዘጋጀውን ሙሉ ፅሁፍ ይመልከቱ። ይህ ማለት በአማርኛ እንደ ኳስ ያሉት ቃላት በአርጎብኛ "ክዋስ" በመባል ይፃፋሉ ማለት ነው።

### *የረዛሚ ድምጾች አጻጻፍ*

አርጎብኛ ረጅም አናባቢዎች የሉትም። ይሁን እንጂ ልክ እንደአማርኛው ረጅም ተናባቢዎች አሉት። ሆኖም አማርኛ እርዝመትን በመደበኛው አፃፃፍ አያሳይም። የአርጎብኛ አፃፃፍ ከአማርኛው በተለየ መልኩ ረጅም ድምፅን እንዲወክል ተደርጓል።*

ለአርጎብኛ ቋንቋም ርዝመትን ለመወከል የሚረዝመውን ድምጽ የሚወክለውን ፊደል ደግሞ (ሁለቴ) ይፃፋል። ይህም ብዙውን ጊዜ ተናባቢን ብቻ በመወከል የሚከሰተውን የሳድስ ፊደል በማስቀደም ቀጥሎ ከአናባቢው አይነት ጋር የሚሄደውን ምልክት መጻፍ ነው። ይሄን በሚከተሉት ምሳሌዎች እናሳያለን።

ምሳሌ:

1. ሀርረሳ 'አረሰ'

2. ሃስሰባ 'አሰበ'

3. ለብበሳ 'ለበሰ'

4. መትተራ 'ቆረጠ'

# ስርአተ ነጥቦችና የቁጥሮች ምልክት

## *የቁጥሮች ምልክት*

አማርኛ ባሁኑ ጊዜ በስፋት የሚጠቀምባቸው ቁጥሮች የአረብኛ አሀዞች የሚባሉት ናቸው:: የግዕዙ የቁጥር ምልክቶች በተወሰኑ ጽሁፎች፣ በተለይ በኦርቶዶክስ ቤተክርስቲያን አካባቢ በሚደረጉ ስራዎች ውስጥ እንጂ በሌሎች ቦታዎች በብዛት በአማርኛ ሲሰራባቸው አይታይም:: በትምህርት ደረጃ ብንመጣ አንድም የሂሳብ ትምህርት በግዕዙ ምልክቶች ሲሰራ አያጋጥመንም:: በርግጥ አማርኛ ብቻ ሳይሆን የተለያዩ ፊደሎችን የሚጠቀሙ የአለማችን በርካታ ቋንቋዎች የሚጠቀሙበት አረባዊ የሚባለውን አህዝ ነው:: ይህ አህዝ በአለማችን ላይ በስፋት ተቀባይነት አግኝቶ (በአማርኛም ጨምሮ) የሚሰራባቸው ዋነኛው ምክንያት ለአጠቃቀም ያለው ምቹነት ነው::

ለአርጎብኛ የተመረጡት የቁጥር ምልክቶች አረባዊ የሚባሉት ሲሆኑ ምልክቶቹም 0፣ 1፣ 2፣ 3፣ 4 ወዘተ. ሲሆኑ በርካታ አሀዞችን ለመወከል በአርጎብኛ ልንጠቀምበት የሚገባውም ይህ የቁጥር አፃፃፍ የሚከተለውን የተለመደውን አፃፃፍ ነው:: ለምሳሌ አንድ ሺህ ለማለት 1000፣ አስራ ሁለት ለማለት 12 ወዘተ.::

## *ስርአተ ነጥብ*

የአርጎብኛ ስርአተ ነጥቦች የሚከተሉት ናቸው፤

1. ነጠላ ሰረዝ ፣
2. ድርብ ሰረዝ ፤
3. አንድ ነጥብ (ነቁጥ) .
8. ንዑስ ክፍተት
9. አቢይ ክፍተት (አዲስ መስመር)
10. ነጠብጣብ (ሶስት ነጥብ) ...

| | |
|---|---|
| 4. አራት ነጥብ ። | 11. ጥያቄ ምልክት ? |
| 5. ሰረዝ (ጭረት) - | 12. ቃል አጋኖ ! |
| 6. የቁም ሰረዝ (ህዝባር) / | 13. ድርብ ትዕምርተ ጥቅስ « » |
| 7. ቅንፍ ( ) | 14. ነጠላ ትዕምርተ ጥቅስ ‘ ’ |

ከላይ ያቀረብናቸው ስርአተ ነጥቦች ሁሉም አማርኛ ባሁኑ ወቅት እየተጠቀመባቸው ያሉ ናቸው። አጠቃቀማቸውን ባማርኛ ውስጥ ካለው ጋር ባንድ አይነት መልኩ ባርጎብኛም ማዋል ከጉዳቱ ይልቅ ጥቅሙ ያመዝናል። ከዚህ በታች የነዚህን ለአርጎብኛ የተመረጡትን ስርአተ ነጥቦች አጠቃቀም (ዋና ዋናዎቹ ግልጋሎቶች ላይ ብቻ በማተኮር) ቀጥለን እናሳያለን።

*ነጠላ ሰረዝ ፣*

ይህን ምልክት በዋናነት ተመሳሳይ የሆኑ ነገሮች ሲዘረዘሩ አንዱን ካንዱ ለመለየት እንጠቀምበታለን። ይህ ስርአተ ነጥብ በአማርኛ እንዳሉት ሌሎች በርካታ አገልግሎቶች በአርጎብኛም ሊውል ይገባል።

*ድርብ ሰረዝ ፤*

ከተራ ቃላትና ሀረግ የበለጡ በዐ.ነገር ደረጃ የሚቀርቡ ተመሳሳይ ነገሮች ሲዘረዘሩ እነሱን ለመለየት እንጠቀምበታለን (ልንጠቀምበት ይገባል)።

*አንድ ነጥብ .*

ምህፃረ ቃላትን ለማመልከት ልንጠቀምበት ይገባል።

*አራት ነጥብ ።*

አረፍተ ነገርን ከአረፍተ ነገር ለመለየት እንጠቀምበታለን።

*ሰረዝ -*

አዳዲስ ጥምር ቃላት ሲፈጠሩ የተጣመሩት ቃላት እንደ አንድ ቃል መግባታቸውን ለማሳየት ይውላል (ወይም ሊውል ይገባዋል)።

*ህዝባር /*

ቀን ሲፃፍ ቀኑን ከወር፣ ወሩን ከአመት ለመለየት ይውላል፡፡

### *ቅንፍ (    )*

«ወይም» የሚለውን በመተካት ይሰራል፡፡

### *ንዑስ ክፍተት*

ቃልን ከቃል ለመለየት ልንገለገልበት ይገባል፡፡

### *አቢይ ክፍተት (አዲስ መስመር)*

አንቀጽን ከአንቀጽ ለመለየት አቢይ ክፍተት መጠቀም ይገባል፡፡ ማለትም ማንኛውም አንቀጽ በአዲስ መስመር መጀመር ይገባዋል ማለት ነው፡፡

### *ነጠብጣብ (...)*

ይህ ምልክት ያልተዘረዘረ ቀጣይ ነገር መኖሩን ለማመልከት ልንገለገልበት ይገባል፡፡

### *ጥያቄ ምልክት ?*

ከቀጥተኛ ጥያቄ በኋላ ይህን ምልክት ልንጠቀምበት ይገባል፡፡

### *ቃል አጋኖ !*

የተጋነኑ፣ የሚያስደንቁ ወዘተ. ሀሳቦችን ለመግለጽ ልንጠቀምበት ይገባል፡፡

### *ድርብ ትዕምርተ ጥቅስ «    »*

በቀጥታ (ቃል በቃል) ያንድን ሌላ ሰው ሀሳብ ስንወስድ የወሰድነውን ሀሳብ በዚህ ምልክት ውስጥ ልናደርግ ይገባል፡፡

### *ነጠላ ትዕምርተ ጥቅስ ‘  ’*

ያንድን ሰው ሀሳብ ቃል በቃል ከሌላ ሰው ስራ ውስጥ ስንወስድ በዚህ በምልክት ውስጥ አባባሉን ልናስቀምጥ ይገባል፡፡

## 1.4. መልመጃ

የሚከተሉትን የአማርኛ ቃላት በአርጎብኛ ፃፏቸው፡፡ ምሳሌ፡-

| | | |
|---|---|---|
| ሀ. ሰደበ | ለ. ጓጉንቸር | መ. ደበደበ |
| ሰድደባ | ግዋጉንቸር | ደበደባ |

1. ሰበረ
2. ገለበጠ
3. ጓንት
4. አገር
5. በኋላ

## ክፍል ሁለት፡ ሰላምታ

በዚህ ክፍል የሰላምታ ልውውጥና መሰነባበትን እንመለከታለን፡፡ በአጠቃላይ መግቢያው ስር እንደገለፅነው አርጎብኛና አማርኛ ካላቸው መቀራረብ በተጨማሪ በአርጎባዎችና በአማራዎች መሀከል ባለው የባህል መቀራረብ የተነሳ የአርጎብኛው ሰላምታ በቀጥታ በአማርኛው መሰረታዊ ፅንሰ ሀሳቡን ሳይለቅ ሊተረጎም ይችላል፡፡(ይህ በእርግጥ በሌሎች በርካታ የኢትዮጵያ ቋንቋዎች መሀከልም ያለ እውነት ነው፡፡) በዚህ የተነሳ ስለ አርጎብኛ ሰላምታዎች ባህላዊ ገፅታ እና አጠቃቀም ከአማርኛው ትርጉም በተጨማሪ ሌላ ማብራሪያ የሚያስፈልገው አይደለም፡፡ ስለዚህም አስፈላጊ መስሎ ሲታየን ብቻ አንዳንድ ነጥቦችን ከማብራራት በስተቀር ሰፊ ማብራሪያ ከመስጠት ተቆጥበናል፡፡

### ሰላምታ ልውውጥ/መለዋወጥ

በዚህ ርዕስ ስር በቅድሚያ በማናቸውም ሰዓት ልንጠቀምበት የምንችለውን የሰላምታ አይነት "አጠቃላይ ሰላምታ" በሚል ርዕስ ስር፣ ከዚያም በተለያዩ ሰዓታት የምንጠቀምባቸውን የሰላምታ ልውውጥ አይነቶች እንመለከታለን፡፡

### *አጠቃላይ ሰላምታ*

እሜቲቱ መሬም፡- አሰላሙ አለይኩም አዮ አህመድ

ወ/ሮ መሬም ፡- ጤና ይስጥልኝ አቶ አህመድ

አዮ አህመድ፡- ወአለይኩም ሠላም እሜቲቱ መሬም

አቶ አህመድ ፡- አብሮ ይስጥልኝ ወ/ሮ መሬም

እሜቲቱ መሬም፡- ወገር ናህ ከሜ ናህ ?

ወ/ሮ መሬም ፡- ደህና ነህ እንደምን ነህ ?

አዮ አህመድ፡ ወገር ነኝ አልሀምዲሊላህ አንች ወገር ኒህ?

አቶ አህመድ፡ ደህና ነኝ ፈጣሪ ይመስገን አንች ደህና ነሽ ?

## *ማብራሪያ*

ከላይ የቀረበው የሰላምታ መለዋወጥ በማናቸውም ሰአት ማለትም ጠዋት ከሰአት ወይም ማታ ሊደረግ የሚችል ብቻ ሳይሆን ይህ ሰላምታ በአንፃራዊ መልኩ ሁለትና ሦስት ቀን ወይም ከዚያ በላይ ሊሆን ይችላል ከተለየ ሰው ጋር የሚደረግ የሰላምታ ልውውጥ ጭምር ነው፡፡ በተለያዩ ፆታዎች፣ ቁጥሮችና በአክብሮት ያለው አጠቃቀም የሚከተለው ነው፡፡

ለወንድ ፆታ፡ ወገር ናህ - ደህና ነህ

ለእንስት ፆታ፡ ወገር ኒህ - ደህና ነሽ

አክብሮት፡ ወገር ኑሁም - ደህና ነዎት/ኖት

ብዙ ቁጥር፡ ወገር ኑሁም - ደህና ናችሁ

## *<u>መሰረታዊ ቃላትና ሀረጎች</u>*

### *<u>ተውላጠ ስሞች</u>*

| <u>አርጎብኛ</u> | <u>አማርኛ</u> |
|---|---|
| እይ/አን/ | እኔ |
| አንክ | አንተ |
| አንች | አንቺ |
| እናንኩም | እናንተ (ለብዙ) |

| | |
|---|---|
| እናንኩም | እርስዎ/አንቱ(ለከቤሬታ) |
| ክሱ | እሱ |
| ክሳ | እሷ |
| እና | እኛ |
| እናንኩም | እናንተ |
| ክሰም | እነሱ (ለብዙ) |
| ክሰም | እሳቸው (ለከበሬታ) |

## ሌሎች ቃላትና ሀረጋት

| አርጎብኛ | አማርኛ |
|---|---|
| ወገር | ደህና |
| አሰላሙ አለይኩም | ጤና ይስጥልኝ/አሰላም አለይኩም |
| አልሀምዱሊላህ | ፈጣሪ ይመስገን |
| አዮ | አቶ |
| እሜቲቱ | ወ/ሮ |
| እሜት | ወ/ት |
| አቮዬ | ማሙሽ |
| እሚሚ | ማሚቱ |
| አዬ | ጋሼ |
| እቱቱ | እትዬ |

## ሰዋሰው

## የመሆን ግስ እርባታ

| አርጎብኛ | አማርኛ |
|---|---|
| ነኝ | ነኝ |
| ናህ | ነህ |
| ኒህ | ነሽ |
| ኑሁም | ናችሁ |

| | |
|---|---|
| ኑሁም | ኖት |
| ኔ | ነው |
| ነድ | ናት |
| ነና | ነን |
| ኑሁም | ናችሁ |
| ኔም | ናቸው |
| ኔም | ናቸው (አክብሮት) |

**መልመጃ**

የሚከተሉትን የሰላምታ ልውውጦች ወደ አርጎብኛ ተርጉሚቸው።

1. አቶ አህመድ፡ ጤና ይስጥልኝ ወ/ሮ መሬም

   ወ/ሮ መሬም፡ አብሮ ይስጥልኝ አቶ አህመድ

   አቶ አህመድ፡ እንደምንነዎት ። ደህና ነዎት?

   ወሮ መሬም፡ ደህና ነኝ ፈጣሪ ይመስገን

2. ሙሳ፡ ጤናይስጥልኝ አንሻ

   አንሻ፡ አብሮ ይስጥልኝ ሙሳ

   ሙሳ፡ እንደምን ነሽ ። ደህና ነሽ?

አንሻ፡ ደህና ነኝ ፈጣሪ ይመስገን አንተ ደህና ነህ ?

## የጥዋት፣ የከሰዓትና የማታ ሰላምታ

### የጥዋት ሰላምታ

እሜቲቱ ሰአዳ፡ ከሜ ሀደርክ አዮ ዘይኑ

ወ/ሮ ሰአዳ ፦ እንደምን አደርክ አቶ ዘይኑ

አዮ ዘይኑ፡ ወገር ነኝ አልህምዱሊላህ። ከሜ ሀደርከም እሜቲቱ ሰአዳ?

አቶ ዘይኑ፡ ደህና ነኝ ፈጣሪ ይመስገን እንደምን አደሩ ወ/ሮ ሰአዳ?

እሜቲቱ ሰአዳ፡ አልህምዱሊላህ።

ወ/ሮ ሰአዳ ፡ ፈጣሪ ይመስገን።

## *ማብራሪያ*

በተለያዩ ሰዎች መካከል ያለው የሰላምታ ልውውጥ የሚከተለው ነው።

1. ሀ. ከሜ ሀደርክ

   እንደምን አደርክ

   ለ. አልሀምዱሊላህ ፡ ከሜ ሀደርክ

   ፈጣሪ ይመስገን ፡ እንደምን አደርክ

2. ሀ. ከሜ ሀደርች

   እንደምን አደርሽ

   ለ. አልሀምዱሊላህ ፡ ወገር ሀደርኩም

   ፈጣሪ ይመስገን ደህና አደሩ

3. ሀ. ከሜ ሀደርኩም

   እንደምን አደሩ

   ለ. አልሀምዱሊላህ

   ፈጣሪ ይመስገን

4. ሀ. ከሜ ሀደርኩም (ለክበሬታ)

   እንደምን አደራችሁ

   ለ. አልሀምዱሊላህ

   ፈጣሪ ይመስገን

## <u>መሰረታዊ ቃላት</u>

| <u>አርጎብኛ</u> | <u>አማርኛ</u> |
|---|---|
| ከሜ | እንደምን |
| ሀደርክ | አደርክ |
| ዛኝ | ንጋት |
| ጥዋህ | ጠዋት ጧት/ጥዋት |
| ቀትር | ቀትር/እኩለ ቀን |

| | |
|---|---|
| ቀና | ቀን |
| ሙሼድ | ማታ |
| ኤታ | ለሊት |
| ዉድቅት | እኩለ ሌሊት |

## ሰዋሰው፡ የሀዳር ግስ እርባታ

| <u>አርጎብኛ</u> | <u>አማርኛ</u> |
|---|---|
| ሀደርኩ | አደርኩ |
| ሀደርን | አደርን |
| ሀደርች | አደርሽ |
| ሀደርኩም | አደራችሁ |
| ሀደራ | አደረ |
| ሀደረድ | አደረች |
| ሀደሩ | አደሩ /ለብዙ/ |
| ሀደሩ | አደሩ(አክብሮት) |

## የቀትር ሰላምታ

ለተለያዩ ሰዎች የሚቀርበው የቀትር ሰላምታ፣ ማለትም ጠዋት ካለፈ በኋላ እስከ ማታ ድረስ ባለው ጊዜ የሚቀርበው ሰላምታ የሚከተለው ነው።

1. ከሜ ዋክ?
   እንደምን ዋልክ?
2. ከሜ ዋች?
   እንደምን ዋልሽ?
3. ከሜ ዋኩም?
   እንደምን ዋሉ?
4. ከሜ ዋኩም?
   እንደምን ዋላችሁ?

**ሰዋሰው**

***የ"ዋለ" ግስ እርባታ***

| አርጎብኛ | አማርኛ |
|---|---|
| ዋኩ | ዋልኩ |
| ዋልን | ዋልን |
| ዋክ | ዋልክ |
| ዋች | ዋልሽ |
| ዋኩም | ዋላችሁ |
| ዋላ | ዋለ |
| ዋለድ | ዋለች |
| ዋሉ | ዋሉ |
| ዋሉ | ዋሉ(አክብሮት) |

***መልመጃ***

ከላይ የቀረቡትን የቀትር ሰላምታ መሰረት በማድርግ ሙሉ የሰላምታ ልውውጥ በአርጎብኛ ስሩ። ትርጉማቸውንም ከስራቸው በአማርኛ መፃፍ አትርሱ።

ምሳሌ፣

እሜቲቱ መሬም፡ ከሜ ዋክ አዮ አህመድ

ወ/ሮ መሬም ፡ እንደምን ዋልክ አቶ አህመድ

አዮ አህመድ፡ አልሀምዱሊላህ:: ከሜ ዋች እሜቲቱ መሬም

አቶ አህመድ፡ ፈጣሪ ይመስገን። እንዴት ዋልሽ ወ/ሮ መሬም

እሜቲቱ መሬም፡ አልሀምዱሊላህ ።

ወ/ሮ መሬም፡ ፈጣሪ ይመስገን።

## *የምሽት ሰላምታ*

በተለያዩ ሰዎች መሀከል የሚደረገው የምሽት ወይም የማታ ሰላምታ የሚከተለው ነው።

1. ከሜ አመሺሀ?

   እንደምን አመሸሽ

2. ከሜ አመሼሀ?

   እንደምን አመሸህ ?

ከሜ አመሼሁም        እንደምን አመሹ

3. ከሜ አመሼሁም ?

   እንደምን አመሹ?

4. ከሜ አመሼሁም ?

   እንደምን አመሻችሁ (ለከበሬታ)

<u>ሰዋሰው</u>

<u>*(የአመሽ ግስ እርባታ)*</u>

| <u>አርጎብኛ</u> | <u>አማርኛ</u> |
|---|---|
| አመሾህ | አመሸሁ |
| አመሼን | አመሸን |
| አመሼህ | አመሸህ |
| አመሺህ | አመሸሽ |
| አመሼሁም | አመሻችሁ |
| አመሼድ | አመሸች |
| አሜሹ | አመሹ |
| አሜሹ | አመሹ(ለአከብሮት) |

<u>መልመጃ</u>

ከላይ የቀረቡትን በተለያዩ ሰዎች መካከል የሚደረጉ የምሽት ሰላምታዎች መሰረት በማድረግ በእያንዳንዳቸው ሙሉ የሰላምታ ልውውጥ ስሩ።

ምሳሌ፣

አዮ አህመድ፡ ከሜ አመሺህ እሜቲቱ መሬም?

አቶ አህመድ ፡ እንደምን አመሸሽ ወሮ መሬም

እሜቲቱ መሬም፡ አልሀምዱሊላሂ ከሜ አሜሼህ አዮ አህመድ

ወ/ሮ መሬም ፡  ደህና ፈጣሪ ይመስገን እንደምን አመሸህ አቶ አህመድ

አዮ አህመድ፡  አልሀምዱሊላህ

አቶ አህመድ ፡ ፈጣሪ ይመስገን

## ስንብት

## *ቀን ላይ መሰነባበት*

1. ወገር ዋል

   ደህና ዋል

2. ወገር ዋይ

   ደህና ዋይ

3. ወገር ዋሉ

   ደህና ዋሉ /ለብዙ/

4. ወገር ዋሉ

   ደህና ዋሉ /ለከበሬታ/

## *የቀን ስንብት መልስ*

1. ወገር ዋል/ዋይ/ዋሉ/ዋሉ

   ደህና ዋል/ዋይ/ዋሉ/ዋሉ

2. ወገር ዋል/ዋይ/ዋሉ

   ደህና ዋል/ዋይ/ዋሉ

3. ወገር ዋል/ዋይ/ዋሉ

ደህና ዋል/ዋይ/ዋሉ

4. ወገር ዋል/ዋይ/ዋሉ

   ደህና ዋል/ዋይ/ዋሉ

## *በምሽት መሰነባበት*

1. ወገር ህደር

   ደህና እደር

2. ወገር ህደሪ

   ደህና እደሪ

3. ወገር ህደሩ

   ደህና እደሩ /ለከበሬታ/

4. ወገር ህደሩ

   ደህና እደሩ /ለብዙ/

## *የምሽት ሰንብት መልስ*

1. ወገር ህደር/ህደሪ/ህደሩ/ህደሩ

   ደህና እደር/እደሪ/እደሩ

2. ወገር ህደር/ህደሪ/ህደሩ

   ደህና እደር/እደሪ/እደሩ/እደሩ

3. ወገር ህደር/ህደሪ//ህደሩ/ህደሩ

   ደህና እደር/እደሪ/እደሩ/እደሩ

4. ወገር ህደር/ህደሪ/ህደሩ/ህደሩ

   ደህና እደር/እደሪ/እደሩ/እደሩ

## *ለረጅም ጊዜ ከሚለይ ሰው መሰነባበት*

1. ወገር ሁን

   ደህና ሁን

2. ወገር ሁኝ

   ደሀና ሁኝ

3. ወገር ሁኑ

   ደሀና ሁኑ /ለብዙ/

4. ወገር ሁኑ

   ደሀን ሁኑ /ለከበሬታ/

## *ለረጅም ጊዜ ለሚለይ ሰው ስንብት መልስ*

1. ወገር ሁን/ሁኝ/ሁኑ/ሁኑ

   ደሀና ሁን/ሁኝ/ሁኑ/ ሁኑ

2. ወገር ሁን/ሁኝ/ሁኑ/ሁኑ

   ደሀና ሁን/ሁኝ/ሁኑ/ ሁኑ

3. ወገር ሁን/ሁኝ/ሁኑ/ሁኑ

   ደሀና ሁን/ሁኝ/ሁኑ/ ሁኑ

4. ወገር ሁን/ሁኝ/ሁኑ/ሁኑ

   ደሀና ሁን/ሁኝ/ሁኑ/ ሁኑ

## ንግግርና ዐ.ነገር ምስረታ

በዚህ ክፍል፣ ከላይ የቀሩቡትን የሰላምታ ልውውጥና ስንብት መሰረት በማድረግ አጫጭር ንግግሮች እንደዚሁም አጫጭር ዐ.ነገር ምስረታዎችን እንመለከታለን፡፡ ወደነዚህ ከማምራታችን በፊት የሚከተሉትን የአርጎብኛ ቃላት ማጥናት ጠቃሚ ነው፡፡

# መሰረታዊ ቃላት

*የሳምንቱ ቀናት*

| አርጎብኛ | አማርኛ |
| --- | --- |
| ሀርጋድ | ሰኞ |

| | |
|---|---|
| ካው | ማክሰኞ |
| አርቢአ | ረቡዕ |
| ኸሚስ | ሀሙስ |
| ጁምዓ | አርብ |
| ሰብት | ቅዳሜ |
| ሰንበድ | እሁድ |

## የአመቱ ወራት

| <u>አርጎብኛ</u> | <u>አማርኛ</u> |
|---|---|
| መሀረም | በጨረቃ አቆጣጠር የዓመቱ የመጀመሪያ ወር |
| ሶፈር | ሁለተኛ ወር |
| ረቢኡል አወል | ሦስተኛ ወር |
| ረቢኡ ሳኒ | አራተኛ ወር |
| ጀማዱል አወል | አምስተኛ ወር |
| ጀማዱ ሳኒ | ስድስተኛ ወር |
| ረጀብ | ሰባተኛ ወር |
| ሻእባን | ስምንተኛ ወር |
| ረመዳን | ዘጠነኛ ወር |
| ሸዋል | አሥረኛ ወር |
| ዙልቃዕዳ | አስራ አንደኛ ወር |
| ዙልሂጃ | አስራ ሁለተኛ ወር |

## የጊዜ አመልካች ቃላትና ሀረጋት

| <u>አርጎብኛ</u> | <u>አማርኛ</u> |
|---|---|
| ወቅት | ጊዜ |
| ሁማ | ዛሬ |
| አ ሀኝ | አሁን |

| | |
|---|---|
| የቀና ቀመድ | እኩለ ቀን |
| ነግ | ነገ |
| ተነግቾጋ/ተነግቦዬ/ | ከነገ ወዲያ |
| ፈጅር | ንጋት |
| ትማይ | ትላንት |
| ተትማይቶጋ/ተትማይቦዬ | ከትላንት ወዲያ |
| ምራህ | ቅድም |
| ወርህ | ወር |
| አመድ | ዓመት |
| ሲስቀና | በቀደም ዕለት |
| ሱየይፍ | ክረምት |
| አልረቢዕ | በጋ |
| ሺታእ | በልግ |
| ኦልኸረፍ | ፀደይ |
| የሁም አመድ | አምና |
| የሁም ኬት አመድ | ሀቻአምና |
| መች | መቼ |

## ሌሎች ቃላት

| አርጎብኛ | አማርኛ |
|---|---|
| ሔዳ | ሄደ |
| መጣ | መጣ |
| እንወዠኹ | እንነጋገር |
| ኦ / ኦን/ | አዎ |
| ደግ | እሺ |
| ሀላ | አለ |
| ኤላዉ | የለም |
| ሆሳ | መጥፎ |

| | |
|---|---|
| መረጮ | ምርጥ |
| ጠራሀ | ጠራ |
| እባኪህ | እባክሽ |
| ጥኑ | ከባድ |
| ኸፊፍ | ቀላል |
| ወገር | ጥሩ |
| እምበር | ነበር |

## ዐ.ነገር ምስረታ

1. ሁማ ሀርጋድ ኔ
   ዛሬ ሰኞ ነው
2. ነግ ሰንበድ ኔ
   ነገ እሁድ ነው።
3. ሱየይፉ ወገር ኔ
   ክረምቱ ጥሩ ነው።
4. የሁም ኬት አመድ ሱየይፉ ያታአብ እምበር
   ሀቻ አምና ክረምቱ ያስቸግር ነበር።
5. አዮ አህመድ ትማይ ሔዳ
   አቶ አህመድ ትላንት ሄደ።
6. እሜት መሬም ከትማይ ቾጋ መጤድ
   ወ/ት መሬም ከትላንትወዲያ መጣች።
7. አንሻ ነግ ትሔደለድ
   አንሻ ነገ ትሄዳለች።

# ንግግር

<u>*ንግግር 1*</u>

አዮ አህመድ፡ ወገር ዋች እሜቲቱ መሬም

አቶ አህመድ ፡ ደህና ዋልሽ ወ/ሮ መሬም

እሜቲቱ መሬም፡ አልሀምዱሊላህ ወገር ዋክ አዮ አህመድ

ወ/ሮ መሬም ፡ ፈጣሪ ይመስገን። ደህና ዋልክ አቶ አህመድ

አዮ አህመድ፡ አልሀምዱሊሎህ አዬ ሙሰጠፋ ሀላ

አቶ አህመድ ፡ ደህና ፈጣሪይመስገን። ጋሽ ሙስጠፋ አለ?

እሜቲቱ  መሬም፡ ሀላ

ወ/ሮ መሬም፡ አለ፡

አዮ አህመድ፡ እባኪህ ጠረሒ

አቶ አህመድ ፡ እባክሽ ጥሪው

እሜቲቱ  መሬም፡ ደግ ወገር ዋል-

እሺ ደህና ዋል

አዮ አህመድ፡ ወገር ዋይ

አቶ አህመድ ፡ ደህና ዋይ።

*<u>ንግግር 2</u>*

አሜቲቱ መሬም፡ ከሜ ሀደርክ አዮ አህመድ ?

ወ/ሮ መሬም ፡ እንደምን አደርክ አቶ አህመድ

አዮ  አህመድ፡ አልሀምዱሊላህ ወገር ሀርደች ?

አቶ አህመድ ፡ ደህና ፈጣሪ  ይመስገን፤ ደህና አደርሽ

እሜቲቱ  መሬም፡ አልሀምዱሊላህ አዬ ሰኢድ መች መጣ

ወ/ሮ መሬም፡  ደህና ፈጣሪ ይመስገን። ጋሽ ሰይድ መቼ መጣ?

አዮ አህመድ፡ ሁማ መጣ

አቶ አህመድ ፡ ዛሬ መጣ

እሜቲቱ መሬም፡ ነግ ጥዋህ እንገናኝ በሌ

ወ/ሮ መሬም ፡ ነገ ጠዋት እንገናኝ በለው

አዮ  አህመድ፡ ደግ ወገር ዋይ

አቶ አህመድ ፡እሺ። ደህና ዋይ

እሜቲቱ  መሬም፡ ወገር ዋል

ወ/ሮ መሬም፡ ደህና ዋል

<u>መልመጃ</u>

ከላይ የቀረቡትን ንግግሮች መሰረት በማድረግ ሁለት አጫጭር ንግግሮች ፃፉ። በምትፅፏቸው ንግግሮች ውስጥ ከላይ በመሰረታዊ ቃላት ስር የተዘረዘሩትን ቃላት ለመጠቀም ሞክሩ።

# ክፍል ሦስት

<u>ሰዋሰው ፡</u>

የሄደና የመጣ ግሶች እርባታ (በሃላፊ ጊዜ)

<u>*የ"ሄደ" ግስ እርባታ*</u>

| <u>አርጎብኛ</u> | <u>አማርኛ</u> |
|---|---|
| ሔድኩ | ሄድኩ |
| ሔድን | ሄድን |
| ሔድክ | ሄድክ |
| ሔድች | ሄድሽ |
| ሔድኩም | ሄዳችሁ |
| ሔዳ | ሄደ |
| ሔደድ | ሄደች |
| ሔዱ | ሄዱ |
| ሔዱ | ሄዱ(ለአክብሮት) |

<u>*የ"መጣ" ግስ እርባታ*</u>

| <u>አርጎብኛ</u> | <u>አማርኛ</u> | |
|---|---|---|
| መጦህ | መጣሁ | |
| | መጤን መጣን | |
| | መጤህ | መጣህ |
| | መጢህ | መጣሽ |
| | መጤሁም | መጣችሁ |

| | | |
|---|---|---|
| መጣ | መጣ | |
| መጤድ | | መጣች |
| መጡ | መጡ | |
| መጡ | መጡ(ለአክብሮት) | |

## በሃላፊ ጊዜ (ያሁንና የወደፊት)

*<u>የ"ሄደ" እርባታ</u>*

| <u>አርጎብኛ</u> | <u>አማርኛ</u> |
|---|---|
| እሔደሉህ | እሄዳለሁ |
| እንሔደልን | እንሄዳለን |
| ትሔደላህ | ትሄዳለህ |
| ትሔጀሊህ | ትሄጃለሽ |
| ትሔደሉሁም | ትሄዳላችሁ |
| ይሐደል | ይሄዳል |
| ትሔደለድ | ትሄዳለች |
| ይሔደሉ | ይሄዳሉ |
| ይሔደሉ | ይሄዳሉ(ለአክብሮት) |

*<u>የ"መጣ" እርባታ</u>*

| <u>አርጎብኛ</u> | <u>አማርኛ</u> |
|---|---|
| እመጠሉህ | እመጣለሁ |
| እንመጠልን | እንመጣለን |
| ትመጠላህ | ትመጣለህ |
| ትመጨሊህ | ትመጪያለሽ |
| ትመጠሉሁም | ትመጣላችሁ |
| ይመጠል | ይመጣል |
| ይመጠሉ | ይመጣሉ(ለአክብሮት) |
| ይመጠሉ | ይመጣሉ |

ትመጠለድ ትመጣለች

<u>መልመጃ</u>

ሀ. የሚከተሉትን አ.ነገሮች ወደ አርጎብኛ ተርጉሚቸው።

1. እኔ ትላንት መጣሁ።
2. አንተ መቼ መጣህ?
3. ወ/ሮ መሬም መቼ ሄደች?
4. ዘንድሮ ፀደዩ ጥሩ ነው።
5. አምና በጋው ጥሩ ነበር።

ለ. የሚከተሉትን ዐ.ነገሮች ወደ አማርኛ ተርጉሚቸው።

1. ኡስታዝ አሸራዬ ሁማ ሔዻ
2. አዮ ሰኢድና እሜት መሬም ትማይ መጡ
3. ነግ ሰንበድ ኔ
4. ሙሼድ እንገናኝ
5. ሷሊህ በቤድ የላዉ

# <u>ክፍል አራት ትውውቅ</u>

*ራስን ማስተዋወቅ*

ሀ. አሰላም አለይኩም
ጤና ይስጥልኝ

ለ. ወአለይኩም ሰላም
አብሮ ይስጥልኝ

ሀ. መሀመድ እቤሔለሉህ
መሀመድ እባላለሁ

ለ. ካሊድ እቤሔለሉህየዠህጠነኛ ክፍል ደረሳ ነኝ

ካሊድ አባላለሁ፤የ9ኛ ክፍል ተማሪ ነኝ።

## <u>መሰረታዊ ቃላት</u>

**ቁጥሮች**

*ተራ ቁጥር*

| *<u>አሃዝ</u>* | *<u>አርጎብኛ</u>* | *<u>አማርኛ</u>* |
|---|---|---|
| 1. | ሀንድ | አንድ |
| 2. | ኬት | ሁለት |
| 3. | ሶስት | ሶስት |
| 4. | አርቢት | አራት |
| 5. | አምስት | አምስት |
| 6. | ስድስት | ስድስት |
| 7. | ሳኢንት | ሰባት |
| 8. | ስምንት | ስምንት |
| 9. | ዥህጠኝ | ዘጠኝ |
| 10. | አስር | አስር |
| 11. | አሰር ሀንድ | አስራ አንድ |
| 20. | ኪያ | ሀያ |
| 21. | ኪያን ሀንድ | ሀያ አንድ |
| 30. | ሷሷ | ሰላሳ |
| 31. | ሷሷን ሀንድ | ሰላሳ አንድ |
| 40. | ሀርቧ | አርባ |
| 41. | ሀርቧን ሀንድ | አርባ አንድ |
| 50. | ሀምሳ | አምሳ |
| 51. | ሀምሳን ሀንድ | አምሳ አንድ |
| 61. | ስልሳ ሀንድ | ስድሳ |
| 70. | ሰብአ | ሰባ |

| | | |
|---|---|---|
| 80. | ሰማንያ | ሰማንያ |
| 90. | ዘጠና | ዘጠና |
| 100. | በቅል | መቶ |
| 1000. | አልፍ/እልፍ | ሺህ |

*ደረጃ ቁጥር*

| <u>አርጎብኛ</u> | <u>አሃዝ</u> | <u>አማርኛ</u> |
|---|---|---|
| ሀንደኛ | 1ኛ | አንደኛ |
| ኬተኛ | 2ኛ | ሁለተኛ |
| ሶስተኛ | 3ኛ | ሶስተኛ |
| አርቢተኛ | 4ኛ | አራተኛ |
| አምስተኛ | 5ኛ | አምስተኛ |
| ስድስተኛ | 6ኛ | ስድስተኛ |
| ሳኢንተኛ | 7ኛ | ሰባተኛ |
| ስምንተኛ | 8ኛ | ስምንተኛ |
| ዝ'ሀጠነኛ | 9ኛ | ዘጠነኛ |
| አስረኛ | 10ኛ | አስረኛ |
| አስር ሀንደኛ | 11ኛ | አስርአንደኛ |
| አስር ኬተኛ | 12ኛ | አስራሁለተኛ |
| አስር ሶስተኛ | 13ኛ | አስራሶስተኛ |
| አሰር አርቢተኛ | 14ኛ | አስራአራተኛ |
| አሰር አምስተኛ | 15ኛ | አስራአምስተኛ |
| አሰር ስድስተኛ | 16ኛ | አስራስድስተኛ |
| አሰር ሳኢንተኛ | 17ኛ | አስራሰባተኛ |
| አሰር ስምንተኛ | 18ኛ | አስራስምንተኛ |
| አሰር ዝ'ሀጠነኛ | 19ኛ | አስራዘጠነኛ |

| | | |
|---|---|---|
| ኪያኛ | 20ኛ | ሃያኛ |
| ኪያን ሀንደኛ | 21ኛ | ሃያአንደኛ |
| ኪያን ኬተኛ | 22ኛ | ሃያሁለተኛ |
| ኪያን ሶስተኛ | 23ኛ | ሃያሶስተኛ |
| ኪያን አርቢተኛ | 24ኛ | ሃያአራተኛ |
| ኪያን አምስተኛ | 25ኛ | ሃያአምስተኛ |

## ሌሎች ቃላት

| አርጎብኛ | አማርኛ |
|---|---|
| እቤሔለሉህ | እባላለሁ |
| ከስብ / ጋር | ስራ |
| ከሰቤ /ጋሬ | ስራዬ |
| ከስባህ /ጋራህ | ስራህ |
| ከስቢህ /ጋሪህ | ስራሽ |
| ከስቧ /ጋርዋ | ስራዋ |
| ቤድ | ቤት |
| ቤዳህ | ቤትህ |
| ቤዲህ | ቤትሽ |
| ቤዴ | ቤቴ |
| ቤዱሁም | ቤትዎ |
| ማንኔ | ማንነዉ |
| ምን/ምንኔ | ምን/ምንድን ነዉ |
| ቼ | የት |
| ጌ | አገር |
| እህ | ወንድም |
| እህድ | እህት |

| | |
|---|---|
| አዉ | አባት |
| ኡምር | እድሜ |
| ክፍል | ክፍል |
| ኮሌጅ | ኮሌጅ |
| ዩኒቨርሲቲ | ዩኒቨርሲቲ |
| ኢስም | ስም |

<u>ሰዋሰው</u>

*አገናዛቢ ተውላጠ ስሞች*

| <u>አርጎብኛ</u> | <u>አማርኛ</u> |
|---|---|
| የእዮ | የእኔ |
| ያንክ | ያንተ |
| ያንች | ያንቺ |
| ይናንኩም | የእርሶ |
| የክሱ | የእርሱ |
| የኮሷ | የእርሷ |
| ይና | የእኛ |
| ይናንኩም | የእናንተ (ለብዙ) |
| ይናንክኩም | የእርሶ (ለክበሬታ) |
| የክሰም | የእነርሱ (ለብዙ) |
| የማን | የማን |
| የክሰም | የእርሳቸው(ለክበሬታ) |
| ኤድኛው | የትኛው (የቱ) |

ከላይ የቀረቡት አገናዛቢ ተውላጠ ስሞች አገባብ ልክ እንደ አማርኛው ነው፡፡ ከሚገናዘበው ስም በፊት ቀድመው ይገባሉ፡፡ የሚከተሉትን ይመልከቱ፤

<u>ምሳሌ</u>፡- <u>አርጎብኛ</u> <u>አማርኛ</u>

| | | |
|---|---|---|
| የእኔ ቤድ ሚፍታህ የሌዉ | የእዮ ቤድ | የእኔ ቤት |
| የእዮእህድ ማህፍላጩድ ኒዶል | የእዮ እህ | የእኔ ወንድ |
| ያንክ ቤድ ይደምቃል | ያንክ ቤድ | የአንተ ቤት |
| ያንክ እህ ኬት ዘዉጅ ሀሌ | ያንክ እህ | የአንተ ወንድም |

ከላይ በምሳሌው የቀረቡት ዐ.ነገሮች ማለትም "የእኔ ቤት"፣ "የአንተ ቤት"፣ “የአንተ ወንድም” ወዘተ እንዳለ አገናዛቢ ስማዊ ሀረጎች ይባላሉ፡፡ እነዚህ አይነት ስማዊ ሀረጎች መሰረታዊ ትርጉማቸውን ሳይለቁ በሌላ መልክ በሁለቱም ቋንቋዎች ሊገለፁ ይችላሉ፤ ለምሳሌ በአማርኛ “የእኔ ቤት” በማለት ፈንታ "ቤቴ" እንደምንለው በአርጎብኛም “የአዮ ቤድ” በማለት ፈንታ "ቤድ" ሊባል ይችላል፡፡ ቤት በሚለው መሰረታዊ ቃል ላይ -ኤ የሚል ቅጥያ ተጨምሮበት ነው ቤቴ የሆነው፡፡ እንደ ኤ አይነቶቹ ቅጥያዎች አገናዛቢ አፀፋ ይባላሉ፡፡ የአርጎብኛን እንደነዚህ አይነቶቹን አፀፋዎች ቀጥለን ከምሳሌ ጋር እናቀርባለን፡፡

## <u>አገናዛቢ አፀፋዎች ከነምሳሌያቸው</u>

| | አገናዛቢ ስማዊ ሀረግ | አገናዛቢ አፀፋዎች | አማርኛ |
|---|---|---|---|
| 1. | አው | | አባት |
| | አዌ | አው-ኤ | አባቴ |
| 2. | ሀርባድ | | አርት |
| | ሀርባዴ | ሀርባድ-ኤ | እራቴ |

በሁሉም መደቦች ያለው እርባታ የሚከተለው ነው፡፡

| | |
|---|---|
| አዌ | አባቴ |
| አውዋህ | አባትህ |
| አውዊህ | አባትሽ |
| አውሁም | አባትዎ |
| አውዋ | አባቷ |

| | |
|---|---|
| አውንዎ | አባታችን |
| አውሁም | አባታችሁ |
| አውወሙ | አባታቸው |
| ሀርባዬ | እራቴ |
| ሀርባዳህ | አራትህ |
| ሀርባዲህ | እራትሽ |
| ሀርባድዎ | እራትዎ |
| ሀርባድዋ | እራትዋ |
| ሀርባዱ | እራቱ |
| ሀርባድሁም | እራታችሁ |
| ሀርባደሙ | እራታአቸው |

<u>መልመጃ</u>

ሀ. "ወንድም" "እህ" የሚለውን ቃል በመውሰድ በሁሉም መደቦች አገናዛቢ አፀፋዎችን በመጨመር አርቡ።

ለ. በሀ ስር በሁሉም መደቦች ላረባችኋቸው፣ ነፃ ተውላጠ ስሞችን ተጠቅማችሁ በምሳሌው መሰረት ስሩ።

ምሳሌ፡ ወንድሜ- የእኔ ወንድም

ቤትህ- የእንተ ቤት

መ. ከአንድ ከማታውቁት ሰው ጋር እንደተገናኛችሁ በመቁጠር ስማችሁን፣ የማን ልጅ እንደሆናችሁ እና እድሜያችሁን በመግለፅ እራሳችሁን በአርጎብኛ አስተዋውቁ።

ረ. የሚከተሉትን ዐ.ነገሮች ወደ አማርኛ ተርጉሟቸው።

1. ትማይ ሊሀዬ ኬት በቅሎ ሀዉኮ
2. ----------------------------------------
3. ----------------------------------------

4. ----------------------------------------

5. ----------------------------------------

6. ----------------------------------------

7. ----------------------------------------

8. ----------------------------------------

9. ----------------------------------------

10. ----------------------------------------

ሰ. የሚከተሉትን ዐ.ነገሮች ወደ አርጎብኛ ተርጉሟቸው፡፡

1. እኔ የ10ኛ ክፍል ተማሪ ነኝ፡፡
2. አባቴ አስተማሪ ነው፡፡
3. እህቴ ነጋዴ ነች፡፡
4. የእናትህ ስራ መንድነን ነው?
5. ስምህ ማነው?
6. አገርህ የት ነው?
7. አህመድ የኮሌጅ ተማሪ ነው፡
8. እድሜህ ስንት ነው?
9. የማን ልጅ ነህ?
10. ስምህ ማነዉ ?

## ሌሎችን ማስተዋወቅ

ሀ. ከሜ ዋክ ኡስታዝ አብዱልከሪም ?
እንደምን ዋልክ መምህር አብዱል ከሪም ?

ለ. አልሀምዱሊላሂ ከሜ ዋክ አዪ ዩሱፍ?
ፈጣሪ ይመስግን እንደምን ዋልክ ጋሽ ዩሱፍ ?

ሐ. ኡንቂ አወል ይቤሔለል ይባላል
ተዋወቁ አወል ይባላል

መ. አሰላም አለይኩም አብዱል ከሪም እቤሔለሉህ

ጤና ይስጥልኝ አብዱል ከሪም እባላለሁ

## *መሰረታዊ ቃላትና ሀረጎች*

### *የሙያ አመልካች ስሞች*

| አርጎብኛ | አማርኛ |
| --- | --- |
| ኡስታዝ | አስተማሪ |
| ደረሳ | ተማሪ |
| አሊም | አዋቂ |
| ጃሂል | ማሀይም |
| አባጋር | የፀሎት መሪ |
| ሀራሽ | ገበሬ |
| አስከር | ወታደር |
| ቦሊስ | ፖሊስ |
| አጣሪ | ነጋዴ |
| የቤድ እመቤት | የቤት እመቤት |
| ሀኪም | ሀኪም |
| ሹፌር | ሹፌር |
| ደዉላ ጋርተኛ | የመንግስት ሰራተኛ |
| ወኪል | ጠበቃ |
| ሀካም | ዳኛ |
| አራሚል | ሴተኛ አዳሪ |
| ገናን | ዘፋኝ/ ድምጻዊ |

<u>መልመጃ</u>

ሀ. ጓደኛችሁን፣ እህታችሁን፣ ወንድማችሁን፣ አባታችሁን ወይም አስተማሪያችሁን ለሌላ ሰው አስተዋውቁ። ሙሉ ንግግሩን በፅሑፍ አቅርቡ።

ለ. የሚከተሉትን ዐ.ነገሮች ወደ አርጎብኛ ተርጉሚቸው

1. አንቺ ተማሪ ነሽ ?

2. እኔ አስተማሪ ነኝ

3. እናንተ ምንድን ናችሁ?

4. እኛ ተማሪዎች ነን፡፡

5. እናንተ ጥሩ አስተማሪዎች ናችሁ

6. እርሷ በሽተኛ ነች፡፡

7. እርሱ ውሽታም ነው፡፡

8. ይህች ልጅ ቆንጆ ነች፡፡

9. ያ ሰው ጉልበት አለው፡፡

10. አቶ ኡመር የመንግስት ሰራተኛ ነው፡፡

ሐ. የሚከተሉትን ዐ.ነገሮች ወደ አማርኛ ተርጉማቸው፡፡

1. እና መጋዳችነና  ሜራች አሁነናው

2. ክሰም እሳምደመል

3. ክስሱ ማስኔ ?

4. አሁኔው ላሀምኔ

5. ክሳ ናሙስ ሀሊያ

6. አለም ሀያእ ሀሌም

7. ሁድ ሱ ይመጤል

## ክፍል አራት፡ የአሉታዊ አ.ነገሮች አመሰራረት

### የአሉታዊ ዐ.ነገሮች አመሰራረት

አሉታዊ አ.ነገሮች በአርጎብኛ የሚመሰረቱት ልክ እንደ አማርኛው ግሶችን በአሉታዊ ቅርፃቸው በመጠቀም ነው፡፡

ለምሳሌ፡-

1. ሀ. አህመድ አስተማሪ ነው

   ለ. አህመድ አስተማሪ አይደለም

2. ሀ. አህመድ አግብቷል

   ለ. አህመድ አላገባም

ከዚህ ቀጥለን የመደበኛ ግሶችን፣ እንዲሁም ከህገ ወጥ ግሶች ውስጥ በጣም ተዘውታሪ የሆኑትን ሶስት ግሶች አሉታዊ ቅርፅን በሁሉም መደቦች በማርባት እንመለከታለን፡፡

## የ"ነው" አሉታዊ እርባታ

| <u>አርጎብኛ</u> | <u>አማርኛ</u> |
|---|---|
| አሁንኩ | አይደለሁም |
| አሆንካው | አይደለህም |
| አሁንቹ | አይደለሽም |
| አሁኔሙ | አይደሉም |
| አሁኔው | አይደለም |
| አህነዱ | አይደለችም |
| አሁነናው | አይደለንም |
| አሁንኩማው | አይደላችሁም |
| አሁኔሙ/አሁኔማው | አይደሉም |

## የአለ (መኖር)አሉታዊ እርባታ

| <u>አርጎብኛ</u> | <u>አማርኛ</u> |
|---|---|
| የሉሁ | የለሁም |
| የለናዉ | የለንም |
| የላሁ | የለህም |
| የሊሁ | የለሽም |
| የሉሁማዉ | የላችሁም |
| የላዉ | የለም |
| የለዱ | የለችም |
| የሉም | የሉም |
| የሉም | የሉም(አክብሮት) |

*የእነዚህ ግሶች አውንታዊ ቅርፆች የሚከተለው ነው፡፡*

| <u>አርጎብኛ</u> | <u>አማርኛ</u> |
|---|---|
| ሀሉህ | አለሁ |
| ሀለን | አለን |
| ሀላህ | አለህ |
| ሀሊህ | አለሽ |
| ሀሉሁም | አላችሁ |
| ሀላ | አለ |
| ሀለድ | አለች |
| ሀሉ | አሉ |
| ሀሉ | አሉ(ለአክብሮት) |

*የአለኝ ግስ አሉታዊ እርባታ*

| <u>አርጎብኛ</u> | <u>አማርኛ</u> |
|---|---|
| የለኙ | የለኝም |
| የለናዉ | የለንም |
| የላሁ | የለህም |
| የሊሁ | የለሽም |
| የሉሁማዉ | የላችሁም |
| የሌዉ | የለውም |
| የሊያዉ | የላትም |
| የሌሙ | የላቸውም |
| የሌሙ | የላቸውም(አክብሮት) |

<u>ከላይ የቀረበው ግስ አውንታዊ ቅርፅ የሚከተለው ነው፡፡</u>

| <u>አርጎብኛ</u> | <u>አማርኛ</u> |
|---|---|
| ሀለኝ | አለኝ |
| ሀለና | አለን |

| | |
|---|---|
| ሀላሀ | አለሀ |
| ሀሊሀ | አለሽ |
| ሀሉሁም | አላችሁ |
| ሀሌ | አለዉ |
| ሀሊያ | አላት |
| ሀሌም | አላቸው |
| ሀሉሁም | አሉት(አክብሮት) |

## የመደበኛ ግስ አሉታዊ እርባታ

| <u>አርጎብኛ</u> | <u>አማርኛ</u> |
|---|---|
| አልዘወጅኩ | አላገባሁም |
| አልዜወጅናዉ | አላገባንም |
| አልዜወጅኩ | አላገባህም |
| አልዜወጅቹ | አላገባሽም |
| አልዜወጅኩማዉ | አላገባችሁም |
| አልዜወጃዉ | አላገባም |
| አልዜወጀቱ | አላገባችም |
| አልዜወጁም | አላገቡም(አክብሮት) |

## የብዙ ቁጥር ምስረታ

| <u>አርጎብኛ</u> | <u>አማርኛ</u> |
|---|---|
| ሌጣ ቁጥር | ነጠላ ቁጥር |
| እሀ | ወንድም |
| እሀድ | እሀት |
| ቤድ | ቤት |
| ጣኢ | ፍየል |
| ደረሳ | ተማሪ |

## ብዙ ቁጥር

| | |
|---|---|
| *እሆች* | *ወንድሞች* |
| እህዳች | እህቶች |
| ቤዳች | ቤቶች |
| ጣኢች | ፍየሎች |
| ደረሳች | ተማሪዎች |

<u>*መልመጃ*</u>

*ሀ.* የሚከተሉትን ዐ.ነገሮች ወደ አርጎብኛ ተረጉሟቸው፡፡

1. አህመድ ብዙ እህቶች አሉት፡፡
2. አህመድ ብዙ ቤቶች አሉት፡፡
3. መሬም ታናሽ እህት አላት፡፡
4. አህመድ  ወንድሞች አሉት፡፡
5. ቤት አለኝ፡፡
6. አህመድ ፍየሎች አሉት፡፡
7. መሬም ባል አላት፡፡
8. መሬም አምና አገባች፡፡
9. አህመድ ትላንት ሚስት አገባ፡፡
10. አህመድ ነጋዴ ወንድም አለው፡፡

ለ. የሚከተሉትን ዐ.ነገሮች ወደ አማርኛ ተርጉሟቸው፡፡

1. መሬም ቲህዋ መስ እሳነድ
2. አህመድ ሊሒዱ ልስ ሸራህ
3. ደረሳች እየሜሔሩ ኔ
4. መሬም ጣኢች ሸረህድ
5. ቤድ መጋር ወገር ኔ
6. አህመድ ብዙህ መጋዳች ሀሊ
7. ትማይ ሊህዬ አርቢት በቅሎ ሀዉኮ

8. በዋድ ኬት አሰድ ጎንጆህ

9. ኬቱ ልጋች ይደምቀሉ

10. ሀንድ ሱ ቀርዶል

መ.. የሚከተሉትን ዐ.ነገሮች ወደ አሉታ ቀይሯቸው፡፡

1. ብዙህ ጣኢች ሀሉኝ

2. ሚስ አግብቸሉህ

3. እህዬ እዘወኛ

4. አህመድ ኡስታዝ እምበራ

5. አህመድ አጣሪ እምበር

## <u>ክፍል አምስት፡ ልዩ ልዩ አገላለፆች</u>

*የሚወዱትንና የሚጠሉትን መግለፅ*

*<u>ንግግር 1</u>*

ሀ. ኑር ሁሴን ሀዩ ትወደላህ

ኑር ሁሴን ወተት ትወዳለህ

ለ. አይ አልወዱ ድምስ ግን እወደሉህ

አይ አልወድም ማር ግን እወዳለሁ

*<u>ንግግር 2</u>*

ሀ. *ቃህዋ* ትወደላህ

ቡና ትወዳለህ

ለ. ኦ/ኦን እጅግ እወደሉህ/ አሻ አልወዱ

አዎ በጣም እወዳለሁ/አይ አልወድም

### *የሚፈልጉትንና የማይፈልጉትን መግለፅ*

*<u>ንግግር 1</u>*

ሀ. ሻሂ ያሀታሀል

ሻይ ትፈልጋለህ

ለ. ኦ/አን እፈልገሉህ /አሻ አይሀተኙ/

አዎ እፈልጋለሁ/ አይ አልፈልግም

***ንግግር 2***

ሀ. ቃህዋ የሃቲኾል

ቡና ትፈልጊያለሽ

ለ. ኦን እፈልገሉህ /አሻ አልፈልጉ/

አዎ እፈልጋለሁ/ አይ አልፈልግም

***ንግግር 3***

ሀ. ሀዩ ያሀቱሁመል?

ወተት ይፈልጋሉ?

ለ. ኦሻ አይሀተኙ

አይ አልፈልግም

## ***መሰረታዊ ቃላት***

## *ምግብና መጠጥ*

| አርጎብኛ | አማርኛ |
|---|---|
| ጋንጀር | እንጀራ |
| እህዋ | ዉሀ |
| ጀው | ሥጋ |
| ድንቡህ | የቅልጥም ቅባት / መቅኒ/ |
| ጊንፎ | ገንፎ |
| ቱማ | ሽንኩርት |
| ድንች | ድንች |

| | |
|---|---|
| ቀይህ ስሬድ | ቀይ ስር |
| አንፋሀና አንቀራ | ጨጓራና ጉበት |
| አንቀራ | ጨጓራ |
| ሀንፊሀ | ጉበት |
| ሙሼ | አንጀት |
| ያልፎራ | ቂጣ |
| ቃሪያ | ቃሪያ |
| ሙዝ | ሙዝ |
| ረጊ | እርጎ |
| ጥሬ ጮው | ጨው |
| ዝግን | ክትፎ |
| ረሀዉ | ረሀብ |
| ባባዬ | ፓፓያ |
| ሎሚ | ሎሚ |
| ማንጎ | ማንጎ |
| ተምር | ቴምር |
| ስኳር ኸላ | ሸንኮራ አገዳ |
| በቆሎ | በቆሎ |
| ድምስ | ማር |
| ቅዊ | ቅቤ |
| ሀዩ | ወተት |
| ቃህዋ | ቡና |
| ሸሞ | ንፍሮ |
| ኩላይ | ኩላሊት |
| አሳ | አሳ |
| ሀምል | ጎመን |
| ሉቅማ | ምግብ |

| | |
|---|---|
| ሶደቃ | /ምጽዋት /ተስካር |
| የስን | ቁርስ |
| ምሳህ | ምሳ |
| ህርባድ | እራት |

## *ሌሎች ቃላት*

| <u>አርጎብኛ</u> | <u>አማርኛ</u> |
|---|---|
| ኦ/ኦን | አዎ |
| ደግ | እሺ |
| አሁኔው | አይደለም |
| ኔ | ነው |

## <u>ሰዋስው</u>

## *አወንታ*

| <u>አርጎብኛ</u> | <u>አማርኛ</u> |
|---|---|
| እወደሉህ | እወዳለሁ |
| ትወደለህ | ትወዳለህ |
| ትወጀሊህ | ትወጃለሽ |
| ይወደል | ይወዳል |
| ትወደለድ | ትወዳለች |
| እንወደልን | እንወዳለን |
| ትወደሉሁሙ | ትወዳላችሁ |
| ይወዶሉ | ይወዳሉ |
| ይወደሉ | ይወዳሉ (አክብሮት) |

## *አሉታ*

| አርጎብኛ | አማርኛ |
|---|---|
| አልወዱ | አልወድም |
| አትወዱ | አትወድም |
| አትወጁ | አትወጅም |
| አይወዱ | አይወድም |
| አትወዱ | አትወድም |
| | |
| አንወዱ | አንወድም |
| አትወዱም | አትወዱም |
| አይወዱም | አይወዱም |
| አይወዱም | አይወዱም(አክብሮት) |

## *አዎንታ*

| አርጎብኛ | አማርኛ |
|---|---|
| ያሀተኚል | እፈልጋለሁ |
| ያሀተናል | እንፈልጋለን |
| ያሀተሀል | ትፈልጋለህ |
| ያሀቲኸል | ትፈልጊያለሽ |
| ያሀቱሁመል | ትፈልጋላችሁ |
| ያሀቴመል | ይፈልጋሉ |
| ያሀቲያል | ትፈልጋለች |
| ያሀቴመል | ይፈልጋሉ |
| ያሀቴመል | ይፈልጋሉ (አክብሮት) |

## *አሉታ*

| አርጎብኛ | አማርኛ |
|---|---|

| | |
|---|---|
| አይሀተኙ | አልፈልግም |
| አይሀተናዉ | አንፈልግም |
| አይሀታሁ | አትፈልግም |
| አይሀቲሁ | አትፈልጊም |
| አይሀቱሁማዉ | አትፈልጉም |
| አይሀቴሙ | አይፈልጉም |
| አይሀታሁ | አትፈልግም |
| አይሀቴዉ | አይፈልግም |
| አይሀቴሙ | አይፈልጉም(አክብሮት) |

***መልመጃ***

ሀ. አንድን ነገር የምትወዱት ወይም የምትጠሉት መሆኑን በመግለፅ አጭር ንግግር ፃፉ፡፡

ለ. አንድን ነገር በመፈለግ ወይም ባለመፈለግ አጭር ንግግር ፃፉ፡፡

## ***መስማማትን ወይም አለመስማማትን መግለፅ***

***ንግግር1***

ሀ. አዮ አህመድ ኡስታዝ ኔ ?

አቶ አህመድ አስተማሪ ነው?

ለ. አሻእአህኔዉ አጣሪ ኔ /ኦ! ኡስታዝ ኔ

አይ አይደለም ነጋዴ ነው፡፡/ አዎ! አስተማሪ ነው፡፡

***ንግግር 2***

ሀ. አንክ የአዮ አህመድ እህ ናህ?

አንተ የአቶ አህመድ ወንድም ነህ?

ለ. ኦን ነኝ

አዎ! ነኝ።

ሀ. እሀህ ቤድ ሀላ?

ወንድምህ ቤት አለ?

ለ. ኦን ሀላ

አዎ አለ።

ሀ. ጥረሔ

ጥራው።

ለ. ደግ

እሺ

<u>መልመጃ</u>

የሚከተሉትን ዐ.ነገሮች በመስማማትና ባለመስማማት ምላሽ ስጡ።

ምሳሌ፡-

1. አንሻ እህትህ ነች?

   አይ! አይደለችም። አዎ! ነች።

2. ሚስት አግባ

   እሺ፡ አገባለሁ።/ አይ፡ አሁን አላገባም።

1. አንክ ኡስታዝ ናህ?

   አንተ አስተማሪ ነህ?

2. አዮ አህመድ ሐራሽ ኔ?

   አቶ አህመድ ገበሬ ነው?

3. መድረሳ መግቢድ ሀለባህ!

   ትምህርት ቤት መግባት አለብህ!

4. አህመድ ፊሲህ ደረሳ ኔ

   አህመድ ጎበዝ ተማሪ ነው።

5. አጣሪ መሆን ወገርኔ
   ነጋዴ መሆን ጥሩ ነው።

## <u>አለመግባባት</u>

### <u>*ንግግር*</u>

ሀ.   ከሜ ሀደርች?
     እንደምን አደርሽ?

ለ.   አልሀምዱሊላህ ወገር ሀደርክ
     ፈጣሪ ይመስገን ደህና አደርክ

ሀ.   አልሀምዱሊላህ ልጋቾችህ ወገር ወገርኔም
     ፈጣሪ ይመስገን፣ ልጆችሽ ደህና ናቸዉ

ለ.   ምን አክ?
     ምን አልክ?

ሀ.   ልጂህ ወገርኔ?
     ልጅሽ ደህና ነው?

ለ.   ኦ! ወገርኔ።
     አዎ! ደህና ነው።

### *ማብራሪያ*

በተለያዩ መደቦች ያለው አጠቃቀም የሚከተለውን ይመስላል።

ምን አች

ምን አልሽ

ምን አኩም

ምን አሉ

ምን አኩም

ምን አላችሁ

ከላይ በምሳሌዎቹ እንደተመለከትነው በመደቦቹ መሃከል ያለው ልዩነት በመጠይቅ ተውላጠ ስሙ ላይ የቅርፅ ለውጥ አያመጣም። የቅርፅ ለውጡ በግሱ ላይ ብቻ የሚታይ ነው።

## ልዩ ልዩ አ.ነገሮች

1. እይ/አን ደረሳ ነኝ ኡስታዝ አሁንኩ

   እኔ ተማሪ ነኝ አስተማሪ አይደለሁም

2. ክሰም ጋርተኛ አሁኔሙ የቀጠር ሱኔም

   እነርሱ ሰራተኛ አይደሉም የውጭ ሰው ናቸው

3. እናንኩም ሀራሻችኍሁም ? ኦን እና ሀራሻች ነና

   እናንተ ገበሬዎች ናችሁ ? አዎ እኛ ገበሬዎች ነን ።

4. እናንኩም እልባችኍሁም? አሻ እልባች አሁነናዉ የሁድ ጌ ሱነና

   እናንተ እንግዳ ናችሁ? እኛ እንግዳ አይደለህንም የዚህ አገር ሰው ነን

## መሰረታዊ ቃላት

| አርጎብኛ | አማርኛ |
|---|---|
| አፎና | ይቅርታ |
| አልሰሞሁ | አልሰማሁም |
| ለቤይክ | አቤት |

### መልመጃ

ሀ. አለመግባባትን የሚያሳይ አንድ አጭር ንግግር ፃፉ።

ለ. የሚከተሉትን ዓርፍተ ነገሮች ወደ አማርኛ ተርጉሟቸው።

1. አንች የጌ ሱኒህ ? አሁንኩ እልባ ነኝ ።
2. እናንኩም መጋር ያሀቱሁመል ? አይሀተናዉ መተኺድ  ኔ የሚያሀተና
3. አንክ ቲና መስትሔደላህ? ቲናንኩም መስ አልሔዱ ረፊቅ ሀለኝ

4. ጂስማህን መናዘህ ያሀታሀል ? አሻ አይሀተኙ እንጄን መመጪድ ኔ ያሀተተኝ
5. እናንኩም የፈረንጅ አፍ ትወንቀሉሁም ? አይ አልወንቅናዉ የአርጎባ አፋኔ የምንወንቂ

## ማብራሪ መጠየቅ

1. ምን ማለታህ ኔ?

   ምን ማለትህ ነው

2. ምን ማለቲህ ኔ?

   ምን ማለትሽ ነው

3. ምን ማለቱሁም ኔ?

   ምን ማለትዎ ነው

4. ምን ማለቱሁም ኔ?

   ምን ማለታችሁ ነው

5. አልገቤኙ?

   አልገባኝም

## መሰረታዊ ቃላትና ሀረጎች

| አርጎብኛ | አማርኛ |
|---|---|
| ምኔ | ምን ነው |
| ምንኔ | ምንድንነዉ |
| ማንኔ | ማን ነው |
| መቼ ኔ | መቼ ነው |
| የማን ኔ | የማን ነው |
| ቼ | የት |
| ከሜ | እንዴት |
| ለምን | ለምን |

**መልመጃ**

ከላይ የቀረቡትን የማብራሪያ መጠየቂያ ቃላትና ሀረጋትን በመጠቀም ሁለት አጫጭር ንግግሮች ፃፉ፡፡

**ልዩ ልዩ ነገሮችን መጠየቅ**

1. ሀ. ሁድ ምንኔ ?

   ይህ ምንድን ነው

   ለ. ሁድ ጋሜላኔ

   ይህ ግመል ነው

2. ሀ. ኦድ ምንኔ ?

   ያ ምንድን ነው

   ለ. ኦድ በጊኔ

   ያ በግ ነው

3. ሀ. ሁለም ምንኔም?

   እነዚህ ምንድን ናቸው

   ለ. ሁለም ቀለማችኔም

   እነዚህ ብዕሮች ናቸው

4. ሀ. ሁለም ምንኔም

   እነዚህ ምንድን ናቸው

   ለ. ሁለም እልባችኔም

   እነዚህ እንግዳዎች ናቸው

5. ሀ. ማንኔ

   ማን ነው

   ለ. ኡስታዝ

   አስተማሪ ነው

6. ሀ. ማን ነድ

   ማን ነች

   ለ. ደረሳ ነድ

   ተማሪ ነች

## <u>መሰረታዊ ቃላትና ሀረጎች</u>

*አመልካች ተውላጠ ስሞች*

### *ሀ. በቅርበት ያለ ነገር (በነጠላ)*

| አርጎብኛ | አማርኛ |
|---|---|
| ሁድ | ይህ |
| ሁይ | ይህች /ይች/ |
| ሁለም | እነዚህ |
| ኦድ | ያ |
| ኦይ | ያች |
| ኦለም | እነዚያ |

### *ለ. በቅርብ ያለ ነገር (ለብዙ)*

| አርጎብኛ | አማርኛ |
|---|---|
| ሁለም | እነዚህ |
| ኦለም | እነዚያ |

## የቤት ቁሳቁሶች

| አርጎብኛ | አማርኛ |
| --- | --- |
| አርቆቢት | ቁምሳጥን |
| መጨጊያ | ወንበር |
| ሙሽማዕ | የመሬት ምንጣፍ |
| | |
| ፍራሽ | ፍራሽ |
| መከዳ | ትራስ |
| ሌማት | መሶብ |
| ማፎሪያ/ሙሀቻ/ | ቡሃቃ |
| ማኅብኅቢያ | ማቅጠኛ |
| የድልህ ጣውራ | የበርበሬ ዕቃ |
| ኮልባ ጣውራ | የፕላስቲክ ዕቃ |
| አቁማዳ | ስልቻ |
| ቃሩራ | ጠርሙስ |
| ፍንጃል | ስኒ |
| ቀርበታ | የውሃ ኮዳ |
| ሚስ | የከብት ቆዳ |
| ተላጅ | ፔርሙዝ |
| ሙሽጥ | ማበጠሪያ |
| ሙቃድ | መብራት |
| ሚርዋህ | ማራገቢያ /ቬንትላተር/ |
| ወሬንጦ | እሾክ ማውጫ |
| መቁረጪድ | መቀስ |
| መሀሮ | ወንፊት |
| መሾድ | ማማሰያ |
| በራድ/እብሪቅ/ | ማንቆርቆሪያ |
| ቢርካ | የዉሀ ማጠራቀሚያ ገንዳ |
| ቴብ | ቴፕ |

| | |
|---|---|
| ሬዲዮን | ሬዲዮ |
| አርኮት | ፍሪጅ |
| ሲልክ | ስልክ |
| ካሚዮን | መኪና |

## *የስውነት አካላት*

| <u>አርጎብኛ</u> | <u>አማርኛ</u> |
|---|---|
| ጅስም | አካል |
| እምቡርጥ | ራቁት ገላ |
| ሩህ | ነፍስ |
| ጅናዛ | አስክሬን |
| ድማህ | ጭንቅላት |
| ጭገር /ደናና/ | ፀጉር |
| ትንት | አፍንጫ |
| ጉንብጭ | ጉንጭ |
| እዝን | ጆሮ |
| ኤን | አይን |
| ከናፍር | ከንፈር |
| ጣድ | ጣት |
| ጭፍር | ጥፍር |
| እዝንጠቂ | ጆሮ ጠቢ |

| | |
|---|---|
| ስን | ጥርስ |
| ሙራጭ | ምራቅ |
| አሪዝ | ጢም |
| ህምብርት | እምብርት |
| ከርስ | ሆድ |
| የከርስ ጣውራ | የሆድ ዕቃ |
| መሰንገሌ | የጎድን አጥንት |
| እንጅ | እጅ |
| እንግር | እግር |
| አሪይ | ክንድ |
| ሰርባ | ቅልጥም |
| ጉልብ | ጉልበት |
| ብዝ | እጢ |
| ኹንሳ | ሴትም ወንድም የሆነ /ፍናፍንት/ |
| ጊሬዶ | ሴታሴት |

## የልየ ልዩ እንሰሳት ሥም

| <u>አርጎብኛ</u> | <u>አማርኛ</u> |
|---|---|
| በሀኢም | እንስሳት |
| አሰድ | አንበሳ |
| ጊዚ | ከብት |
| ጋሜላ | ግመል |
| አንስያ | አህያ |
| በራ | በሬ |
| በጊ | በግ |
| ጣኢ | ፍየል |
| ጁቺ | ጅብ |
| ዶሮ | ዶሮ |

| | |
|---|---|
| አንጢያ | ድመት |
| ሄንጥ | አይጥ |
| ህዋው | እባብ |
| ሀመጁል መሀጅ | አርአንክብል |

## አልባሳት

| <u>አርጎብኛ</u> | <u>አማርኛ</u> |
|---|---|
| ግልድም/ መርጦ/ መስነፍ / | ሸርጥ |
| ሰናፊል | ሱሪ |
| ጉፍታ | የባለ ትዳር ሴት ካባ |
| ጦሊት | ፎጣ |
| ጥቡቆ | የህፃናት ልብስ |
| ጥሙር /ኹፍ/ | ጫማ |
| ባርኔጣ | ኮፊያ |
| መካቻ | መታጠቂያ |

<u>**መልመጃ**</u>

*ሀ. የሚከተሉቱን ዐ. ነገሮች ወደ አማርኛ ተርጉሟቸው፡፡*

1. *ሀ. ሁለም ምንነኔም?*

   *ለ. ሁለም ጊዚች ኔም*

2. *ሀ. ኦድ ምንኔ ?*

ለ. ኦድ ስራይ ኔ

3. ሀ. ሁድ ምንኔ ?

ለ. ሁድ ሀርጥኔ

4. ሀ. ማንኔ? ደረሳ ኔ

ለ. ደረሳ ኔ

5. ሀ. ኦለም ምንኔም ?

ለ. ኦለም አሽርጌታችኔም

ለ. የሚከተሉትን ዐ.ነገሮች ወደ አርጎብኛ ተርጉሚቸው፡፡

1. ሀ. ያ ምንድን ነው ?

ለ. ያ ስዕል ነው፡፡

2. ሀ. እርሱ ምንድን ነው?

ለ. ይህ መጽሐፍ ነው፡፡

3. ሀ. እነዚያ ምንድን ናቸው?

ለ. እነዚያ አይጦች ናቸው፡፡

4. ሀ. እነርሱ ምንድን ናቸው?

ለ. እነርሱ ሰዎች ናቸው፡፡

## ክፍል ስድስት፡ ግብይት

### *ንግግር 1*

ገዢ፡ ቱማ ስንት ኔ

ሽንኩርት ስንት ነው?

ሻጭ፡ ቱማ በኪሎ ኬት ቀርሽ ኔ

ሽንኩርት በኪሎ 2 ብር ነው፡፡

ገዢ፡ ሀንድ ቀርሽ ተቀመድ /ኬት አላድ ልሽርሀህ ?

አንድ ብር ከሃምሳ ልግዛህ?

ሻጭ፡ አይሽጡ

አይሸጥም።

ገዢ፡ ደግ ኬት ኪሎ ሀወኝ

እሺ ሁለት ኪሎ ስጠኝ

*__ንግግር 2__*

ገዥ፡ ሁድ ባራ ስንት ኔ

ይህ በሬ ስንት ነው?

ሻጭ፡ ኬት እልፍ ቀርሽ

ሁለት ሺህ ብር

ገዥ፡ ሀንድ እልፍ ከዠህጠኝ ብቅል ልሽርሀህ?

አንድ ሺህ ዘጠኝ መቶ ልግዛልህ?

ሻጭ፡ ደግ ሽርሔ

እሺ ግዛው/ውሰደው

## *__መሰረታዊ ቃላትና ሐረጎች__*

## *የሳንቲሞችና የብሮች አቆጣጠር*

| <u>አርጎብኛ</u> | <u>አማርኛ</u> |
| --- | --- |
| ቀርሽ | ብር |
| ፍራንክ | ሳንቲም |
| ኬት ፍራንክ | አምስት ሳንቲም |
| አርቢት ፍራንክ | አስር ሳንቲም |
| ስድስት ፍራንክ | አስራ አምስት ሳንቲም |
| ስምንት ፍራንክ | ሀያ ሳንቲም |
| ስሙኒ | ሀያ አምስት ሳንቲም |
| ስሙኒ ተሁለት ፍራንክ | ሰላሳ ሳንቲም |
| ስሙኒ ተአራት ፍራንክ | ሰላሳ አምስት ሳንቲም |

| | |
|---|---|
| ሽልንግ | አምሳ ሳንቲም |
| ሽልንግ ተሁለት ፍራንክ | አምሳ አምስት ሳንቲም |
| አላድ/ሩብያ/ሽልንግ ተስሙኒ | ሰባ አምስት ሳንቲም |
| ሀንድ ቀርሽ | አንድ ብር |
| ሀንድ ቀርሽ ተሽልንግ | አንድ ብር ከአምሳ ሳንቲም |
| ሀንድ ቀርሽ ተሽልንግ ተሁለት ፍራንክ | አንድ ብር ከስልሳ አምስት ሳንቲም |
| ባወንድ | አስር ብር |
| ብቅል | መቶ ብር |
| እልፍ /አልፋ/ | ሺህ |
| ሚሊዮን | ሚሊዮን |

## *ሌሎች ቃላት*

| <u>አርጎብኛ</u> | <u>አማርኛ</u> |
|---|---|
| ሽረሀ | ገዛ |
| ሽጣ | ሸጠ |
| አገና | ዋጋ |
| ኪሎ | ኪሎ |
| አሔዳ | ወሰደው |

## <u>ሰዋስው</u>

## *አፀፋ ተውላጠ ስሞች*

| <u>አርጎብኛ</u> | <u>አማርኛ</u> |
|---|---|
| ነብስኖ | ራሳችን |
| ነብሴ | ራሴ |
| ነብሳህ | ራስህ |
| ነብሲህ | ራስሽ |
| ነብሱ | ራሱ |
| ነብሷ | ራሷ |

ነብሱሁም ራሳችሁ (ለብዙ)

ነብስሁም ራሳችሁ (ለከበሬታ)

ከላይ የቀረቡትን አፀፋ ተውላጠ ስሞች አጠቃቀም በሚከተሉቱት ዓ.ነገሮች ምሳሌነት እንመልከት፡፡

1. ነብሳህ መጥዳህ ጣውራውን አሒድ

   እራስህ መጥተህ ዕቃውን ውሰድ
2. ነብሷ አዊዳቴ ወሌ ነደመድ
   እራሷ ነግራው ደግሞ ተቆጨች
3. ነብስኖን በነብስኖ ልማኽዳደር ችልደነል

   ራሳችንን በራሳችን ለማስተዳደር ችለናል

4. ነብሱሁም በጋርኩሚ ቤድ አርግዙ
   እራሳችሁ በሰራችሁት ቤት ተቀመጠ

<u>መልመጃ</u>

ሀ. የሚከተሉት ዐ.ነገሮች ወደ አርጎብኛ ተርጉሚቸው፡፡

1. ራሷ አይታ ገዛች

2. ራሳቸው መጥተው ይዩት

3. ራሴ የአደራ ገንዘብ ሰጥቼው አላውቅም አለ

4. ራሱ በሰራው ወንበር ላይ ተቀምጧል

5. ይህንን ቁምሳጥን እኔ ራሴ ነው የሰራሁት

ለ. የሚከተሉት ዐ.ነገሮች ወደ አማርኛ ተርጉማቸው።

1. ነብሱሁም ሔዱሁም ካልጋሀርኩሚ ጋሩ ይበላሽል

2. ነብሱሁም ታልዋዤሁም ማም አይዋዥሉሁም

3. ነብሷ እናዝህዳ ክሰምን ከለከለቴም

4 . ነብሲህ ታላዋዤሒ በጆ አይሉ

5. ነብሰሙ ባመጢ ታአብ መከራሙን ያሀንጆሉ

መ. የሚከተሉትን የብርና የሳንቲም መጠን በአርጎብኛ ፃፉ።

1. ሰላሳ አምስት ሳንቲም
2. አምሳ አምስት ሳንቲም
3. ዘጠና ሳንቲም
4. አንድ ብር
5. አንድብር ከአስራ አምስት ሳንቲም
6. ብር ከአምሳ ሳንቲም
7. ብር ከሳባ አምስት ሳንቲም
8. ሁለት መቶ ብር
9. ሶስት ሺህ ብር
10. አራት ሚሊዮን ብር

ረ. ሁለት ሰዎች ሲገበያዩ የሚያሳይ አንድ አጭር ንግግር ፃፉ።

## ክፍል ሰባት፡ አቅጣጫ መጠየቅ

### አ.ነገር ምስረታ

1. በአፎንቻ ሌፍ ካሚዎል ቆምዶል
   ከቤት ውጭ መኪና ቆሟል
2. ተወንበሩ ስሬድ ኪታብ ሀላ
   ከወንበሩ ስር መፅሀፍ አለ
3. በዛፉ ሌፍ ቆምዶል
   በዛፉ ላይ ቆሟል
4. በቅሎ ሌፍ አርግዝዶል
   በቅሎ ላይ ተቀምጧል
5. በእንግሬ ስሬድ ወደቃ
   እግሬ ስር ወደቀ

### *ንግግር 1*

ሀ. አሰላሙ አለይኩም
ጤና ይስጥልኝ፡፡

ለ. ወአለይኩሙ ሰላም
አብሮ ይስጥልኝ፡፡

ሀ. ሸንኬ ተከሚሴ ቼጋኔ
ሸንኬ ከከሚሴ ወዴት ይገኛል፡፡

ለ. ሸንኬ ተከሚሴ በሸርቅ ይገኝል
ሸንኬ ከከሚሴ ወደምስራቅ ይገኛል፡፡

ሀ. ሹክረን
አመሰግናለሁ

ለ. አፍወን
ምንም አይደል

## *ንግግር 2*

ሀ. አሰላሙ አለይኩም

ጤና ይስጥልኝ።

ለ. ወአለይኩሙ ሰላም

አብሮ ይስጥልኝ

ሀ. የእሜት ዘህራ ቤድ ቼጋኔ

የወ/ት ዘሀራ ቤት ወዴት ነው?

ለ. ተሁድ ዘር በሌፍኔ

ከዚህ ወንዝ በላይ ነው።

ሀ. ሹክረን

አመሰግናለሁ።

ለ. አፍወን

ምንም አይደል።

## *መሰረታዊ ቃላትና ሀረጎች*

### *አቅጣጫዎች*

| አርጎብኛ | አማርኛ |
|---|---|
| ሸርቅ | ምስራቅ |
| ገርብ | ምዕራብ |
| ቂብላ | ሰሜን |
| ጁኑብ | ደቡብ |

## *ልዩ ልዩ ቃላትና ሀረጋት*

| አርጎብኛ | አማርኛ |
|---|---|
| ጨሄድ | ፀሐይ |
| ሒላል | ጨረቃ |
| ቸቸሀ | ኮከብ |
| አዛኝቸቸሀ | የአጥቢያ ኮከብ |
| ሀዋዕ | አየር |
| ሰማዕ | ሰማይ |
| በርቅ | ብልጭታ |
| አዶና | ደመና |
| መውጅ | ማዕበል |
| ሳልጅ | የበረዶ ክምር |
| ጀበል | ተራራ |
| ሙሒጥ | ዉቅያኖስ |
| ዘር | ወንዝ |
| ሀሮዬ | ኩሬ |
| ጊንጀላ/ሀጀር/ | ድንጋይ |
| ገበላ | ገደል |
| ሌፉን | ላዩን |
| ቴፉን | ታቹን |
| የሌፎቹ | የላዮቹ |
| የሩሾቹ | የላዮቹ |
| የሩሽ ገንዳ | የላዮቹ ሰፈሮች |
| የሌፍ ገንዳ | የላዮቹ ሰፈሮች |
| የቴፍ ገንዳ | የታቾቹ ሰፈሮች |
| ይና ገንዳች | የእዚህ ሰፈሮች |
| ሁሉም ገንዳች | የእነዚህ ሰፈሮች |
| የኦላም ገንዳች | የእነዚያ ሰፈሮች |

የሁድ ገንዳች የዚሀ ሰፌሮች

<u>መልመጃ</u>

ሀ. የሚከተሉትን ዓ.ነገሮች ወደ አርጎብኛ ተርጉሚቸው።

1. የላይ ሰፈር ሰዎች እዚህ ይመጣሉ።
2. ፀሀይ በምስራቅ ትወጣለች።
3. በደቡብ በኩል የምትታየው ኮከብ ደማቅ ነች።
4. የአቶ ኡመር ቤት በደቡብ አዲስ አበባ ነው።
5 . ከዚህ በታች ወንዝ አለ።
6 . ከዉቅያኖሱ በላይ የበረዶ ክምር ይታያል።
7 . ኩሬዉ ሞልቶ ወደ ገደሉ እየፈሰሰ ነዉ።

ለ. የሚከተሉትን ዓ.ነገሮች ወደ አማርኛ ተርጉሚቸው።

1. አሊም ሱቻች ወደ ሒላል ና ቸቸሀ ደርስደመል ይቤሔል
2. የሌፍ ገንዳ ሱቻች ወደ ጀበል እየወጡ ኔ
3. ወደ ቂብላ የሀላዉ ሀዋእ ኦደና ሀሌ
4. የሁድ ገንዳ ሱቻች መዉጅ ሚጥዶዬም ይወንቀል
5. ጬሑድ በገርብ ትጠልቀለድ

## <u>ክፍል ስምንት፡ የጊዜ ስርአት (Tenses)</u>

አርጎብኛ እንደአማርኛ ስድስት የጊዜ አይነቶች አሉት።* እነሱም የዋህ ሀላፊ፣ የማያቋርጥ ሀላፊ፣ “ውጤት” (perfect) ሀላፊ፣ የዋህ ኢ-ሀላፊ (የአሁን/ የትንቢት)፣ የማያቋርጥ ኢ-ሀላፊና “ውጤት” ኢ-ሀላፊ (ውጤት አሁን) ጊዜያት ናቸው። እነዚህ በእንግሊዘኛ እንደቅድምተከተላቸው simple past, past continuous, past perfect, simple non-past, present continuous and present perfect የሚባሉት ናቸው። እነዚህ የጊዜ አይነቶች

የሚመሰረቱት የግሶቹን ቅርፅ በመለዋወጥ እና ረዳት ግሶችን በመጠቀም ነው። የእያንዳንዳቸውን አመሰራረት ከዚህ ቀጥለን እናቀርባለን።

## 1. የዋህ ሀላፊ

የሚከተሉት ዓ.ነገሮች የዋህ ሀላፊ ጊዜን የሚመለከቱ ናቸው።

1. አዮ አህመድ አሰከር እምበሩ
   አቶ አህመድ ወታደር ነበሩ።
2. አዮ አህመድ ባራ ሸረሁ
   አቶ አህመድ በሬ ገዙ።
3. እሜት መሬም ልጁን አሔደቴ
   ወ/ት መሬም ልጁን ወሰደችው።
4. መሬም ደረሳ አገቤድ
   መሬም ተማሪ አገባች።
5. ኡመር ወደ ቤዱ ሔዳ
   ኡመር ወደ ቤቱ ሄደ።

ከላይ ለመግለፅ እንደሞከርነው በተለያዩ ግዜያት መሀከል ያለው መሰረታዊ ሰዋሰዋዊ ልዩነት የሚንፀባርቀው በግሶች ላይ ነው። መደበኛ ግሶች ያላቸው የየዋህ ሀላፊ ቅርፅን ሁለት ግሶችን በመውሰድ በሁሉም መደቦች እርባታቸውን እናሳያነለን።

## የአላፊ ግሶች ቅርፅ (የመደብ እርባታ)

| <u>አርጎብኛ</u> | <u>አማርኛ</u> |
|---|---|
| ግስ፡ ሀዋ | ሰጠ |
| ሀውኩ | ሰጠሁ |
| ሀውክ | ሰጠህ |
| ሀውች | ሰጠሽ |
| ሀዋ | ሰጠ |

| | |
|---|---|
| ሀወድ | ሰጠች |
| ሀውን | ሰጠን |
| ሀውኩም | ሰጣችሁ |
| ሀው | ሰጡ |
| ሀው | ሰጡ |
| ግስ፡ አሔደ | ወሰደ |
| አሔድኩ | ወሰድሁ |
| አሔድክ | ወሰድህ |
| አሔድች | ወሰድሽ |
| አሔዳ | ወሰደ |
| አሔደድ | ወሰደች |
| አሔድን | ወሰድን |
| አሔድኩም | ወሰዳችሁ |
| አሔዱ | ወሰዱ /ለብዙ/ |
| አሔዱ | ወሰዱ /ለከበሬታ/ |

## “ውጤት” ሀላፊ ጊዜ / past perfect tense

ይህ የአርጎብኛው የጊዜ ስርዓት ከእንግሊዘኛው “past perfect tense” ጋር ተመሳሳይነት አለው። ከአማርኛው ውጤት ሃላፊ ጊዜ ጋር ያለው ተመሳሳይነት በሚሰጠው ትርጉም ወይም ፍቺ ብቻ ሳይሆን በአመሰራረት ረገድም ነው። የሚከተሉት ዓ.ነገሮች ይህን የጊዜ ስርዓት የሚያመለክቱ ናቸው።

1. አዮ ኡመር ምሳሁን በልዶ እምበር
   አቶ ኡመር ምሳውን በልቶ ነበር
2. እሜት ሰአዳ ትናንት መጥታ ነበር
   ወ/ት ሰአዳ ትናት መጥታ ነበር

3. አንሻ ጎዜ ሔዳ እምበር

   አንሻ ጎዜ ሄዳ ነበር

4. ሙሳ ሳሪቅ እምበራ

   ሙሳ ሌባ ነበር

5. አህመድ ፈሲህ ደረሳ እምበራ

   አህመድ ጎበዝ ተማሪ ነበር

## <u>የውጤት ሀላፊ (past perfect) የግሶች ቅርፅ /እርባታ</u>

| <u>አርጎብኛ</u> | <u>አማርኛ</u> |
|---|---|
| ሀውች እምበር | ሰጥቼ ነበር |
| ሀውዳህ እምበር | ሰጥተህ ነበር |
| ሀውዲህ እምበር | ሰጥተሽ ነበር |
| ሀውዶ እምበር | ሰጥቶ ነበር |
| ሀውዳ እምበር | ሰጥታ ነበር |
| ሀውደን እምበር | ሰጥተን ነበር |
| ሀውዱሁም እምበር | ሰጥታችሁ ነበር |
| ሀውደም እምበር | ሰጥተው ነበር /ለብዙ/ |
| ሀውደም እምበር | ሰጥተው ነበር /ለከበሬታ |

## <u>የማያቋርጥ ሀላፊ</u>

የማያቋርጥ ሀላፊ ጊዜ በአርጎብኛ የሚመሰረተው በመደበኛው ግስ ኢ-ሀላፊ ቅርፅ ላይ “እምበር” “ነበር” የሚለውን ረዳት ግስ በመጨመር ነው፡፡ ይህን ጊዜ የሚያመለክቱ ዓ.ነገሮች የሚከተሉት አይነት ናቸው፡፡

1. ሀሊማ ምሳሁዋን እየበሌድ ኔ
   ሀሊማ ምሳዋን እየበላች ነበር፡፡
2. ሰኢድ ወደ አልዩ ጌ እየሔዳ እምበር
   ሰኢድ ወደ ናዝሬት እየሄደ ነበር፡፡
3. አሚራ ኪታብ እየሸርህች ኔ
   አሚራ መፅሀፍ እየገዛ ነበር፡፡
4. ራዲ እየመጤድ እምበር
   ራዲ እየመጣች ነበር፡፡
5. መሬም ጋንጀር እየጋገረድ እምበር
   መሬም እንጀራ እየጋገረች ነበር፡፡

ከላይ በምሳሌ አ.ነገሮቹ እንደምንመለከተው በየማያቋርጥ ሀላፊ ጊዜ ባለቤትን የሚያመለክቱት አፀፋዎቹ የሚጨምሩበት ልክ እንደአማርኛው በዋናው ግስ ላይ ነው፡፡ ረዳት ግሱ ቅርፁን ለተለያዩ መደቦች አይለውጥም፡፡ በሁሉም መደቦች ያለውን እርባታ ‘አሔዳ’ ‘ወሰደ‘ የሚለውን ግስ ወስደን ቀጥለን እናሳያለን፡፡

## በየማያቋርጥ ሀላፊ የግሶች ቅርፅ

| | አርጎብኛ | አማርኛ |
|---|---|---|
| ግስ፡ | አሔደ | ወሰደ |
| | አሔድ እምበር | እወስድ ነበር |
| | ታሔድ እምበር | ትወስድ ነበር |
| | ታሔጂ እምበር | ትወስጂ ነበር |
| | ያሔድ እምበር | ይወስድ ነበር |
| | ታሔድ እምበር | ትወስድ ነበር |

እናሔድ እምበር እንወስድ ነበር

ታሔዱ እምበር ትወስዱ ነበር

ያሔዱ እምበር ይወስዱ ነበር /ለብዙ/

ያሔዱ እምበር ይወስዱ ነበር /ለከበሬታ/

ከላይ ለመገንዘብ እንደሚቻለው የማያቋርጥ ሀላፊና ውጤት ሀላፊ የሚለያዩት በዋነኛው ግስ ቅርፅ ብቻ ነው፡፡ ዋናው ግስ በውጤት ሃላፊ በአማርኛና በግዕዝ ሰዋሰው ቦዝ አንቀፅ የሚባለውን ቅርፅ የሚይዝ ሲሆን በየማያቋርጥ ሃላፊ ግን የዋህ ኢ-ሀላፊን ወይም "ኢ"-ፍጹም እስፔክት የሚባለውን ቅርፅ ይይዛል፡፡ ከዚህ ውጪ በሁለቱም የጊዜ አይነቶች ረዳት ግስ የሚጨምር ሲሆን ረዳት ግሱም “እምበር” ነው፡፡ ይህ ረዳት ግስም በሁለቱም የጊዜ አይነቶች ለተለያዩ መደቦች ቅርፁን አይለውጥም፡፡ “ሀዋ” ‘ሰጠ’ የሚለውን ግስ በመውሰድ በዚህ የጊዜ ስርዓት በሁሉም መደቦች የሚኖረውን ቅርፅ ከረዳት ግሱ ጋር አጣምረን እናቀርባለን፡፡

## <u>የዋህ ኢ-ሀላፊ ጊዜ (simple non-past)</u>

ከላይ እንደተገለፀው አርጎብኛ ያሉት መሰረታዊ የጊዜ ዓይነቶች ሁለት ናቸው፡፡ በዚህ ምክንያት እንደ እንግሊዘኛ እና እንደ አንዳንድ የጉራጌ ቋንቋዎች የዋህ የአሁን ጊዜ “<u>simple present tense</u>” እና የዋህ የወደፊት ጊዜ “<u>simple future tense</u>” የሚባሉ ጊዜያት የሉትም፡፡ እነዚህ ጊዜያት በአርጎብኛ ልክ እንደ አማርኛው በአንድ ሰዋሰዋዊ ቅርጽ ነው የሚገለፁት፡፡ ለዚህም ነው እነዚህን ጊዜያት የሚያመለክተውን ቅርፅ የዋህ ኢ-ሀላፊ የምንለው፡፡ የሚከተሉት ዓ.ነገሮች የየዋህ ኢ-ሀላፊ ምሳሌዎች ናቸው፡፡

1. ኡመር ወደ ቤድ ይሔደል
   ኡመር ወደቤት ይሄዳል
2. ሀሊማ ናዝሬት ትሔደለድ
   ሀሊማ ናዝሬት ትሄዳለች
3. ሰኢድ ኮረሜ ይመጣል
   ሰኢድ ኮረሜ ይመጣል

4. አህመድ ፈሲህ ደረሳ ኔ

አህመድ ጎበዝ ተማሪ ነው።

5. መሬም በቤድ ዉስጥ ሀለድ

መሬም እቤት ውስጥ አለች።

በየዋሀ- ኢሀላፊ መደበኛ ግሶች ለተለያዩ መደቦች የሚያደርጉት እርባታን ከዚህ ቀጥለን ሁለት ግሶች በምሳሌነት በመውሰድ እናሳያለን።

## <u>የየዋሀ ኢ ሀላፊ የግሶች እርባታ</u>

| <u>አርጎብኛ</u> | <u>አማርኛ</u> |
|---|---|
| ግስ፡ ሸቻ | ጠጣ |
| እሸቻሉሀ | እጠጣለሁ |
| ትሸቻላሀ | ትጠጣለህ |
| ትሸቻሊሀ | ትጠጫለሽ |
| ይሸቻል | ይጠጣል |
| ትሸቻለድ | ትጠጣለች |
| እንሸቻልን | እንጠጣለን |
| ትሸቻሉሁም | ትጠጣላችሁ |
| ይሸቻሉ | ይጠጣሉ |

| ግስ፡ አሔዳ | ወሰደ |
|---|---|
| አሔደሉህ | እወስዳለሁ |
| ታሔደላህ | ትወስዳለህ |
| ታሔጀሊህ | ትወስጃለሽ |
| ያሔደል | ይወስዳል |
| ታሔደለድ | ትወስዳለች |
| እናሔደልን | እንወስዳለን |
| ታሔደሉሁም | ትወስዳለችሁ |
| ያሔደሉ | ይወስዳሉ (ለብዙ) |
| ያሔደሉ | ይወስዳሉ (ለከበሬታ) |

## “ውጤት” ያሁን ግዜ (Present Perfect Tense)

ይህ የጊዜ አይነት ከውጤት ሀላፊ ጊዜ የሚለየው በስተመጨረሻ በሚገባው ረዳት ግስ ብቻ ነው፡፡ በዚህ የጊዜ ስርዓት በ “እምበር” ፈንታ እስር የሆነ ያሁን ጊዜ አመልካች ረዳት ግስ ይገባል፡፡ የሚከተሉትን ምሳሌዎች እንመልከት፡፡

1. ኡመር መጥዶል

   ኡመር መጥቷል፡፡

2. መሬም ሔዳለድ

መሬም ሄዳለች።

3. አንሻ ምሳሁዋን በልዳለድ

   አንሻ ምሳዋን በልታለች።

4. አዮ አህመድ ኪታቡን አሒዶል

   አቶ አህመድ መፅሀፉን ወስደዋል።

5. ያሲን አሰድ ገድልዶል

   ያሲን አንበሳ ገድሏል።

በውጤት ያሁን (**Present Perfect**) ጊዜ የግሶች የመደብ እርባታ የሚከተለውን ይመስላል።

## የውጤት ሀላፊ ግሶች እርባታ

| አርጎብኛ | አማርኛ |
|---|---|
| ግስ፡ ሀዋ | ሰጠ |
| ሀውቾሉህ | ስጥቿያለሁ |
| ሀውዳሀል/ሀውደከል | ሰጥተሀል |
| ሀውዲኸል | ሰጥተሻል |
| ሀውዶል | ሰጥቷል |
| ሀውዳለድ | ሰጥታለች |
| ሀውደነል | ሰጥተናል |
| ሀውዱሁመል | ሰጥታችኋል |

| | |
|---|---|
| ሀውደመል | ሰጥተዋል (ለከበሬታ) |
| ሀውደመል | ሰጥተዋል (ለብዙ) |

| | |
|---|---|
| ግስ፡ ሽቻ | ጠጣ |
| ሽችቸሉህ | ጠጥቺያለሁ |
| ሽችደሀል | ጠጥተሀል |
| ሽችዲኽል | ጠጥተሻል |
| ሽችዶል | ጠጥቷል |
| ሽችዳለድ | ጠጥታለች |
| ሽችደነል | ጠጥተናል |
| ሽችዱሁመል | ጠጥታችዋል |
| ሽችደመል | ጠጥተዋል /ለብዙ/ |
| ሽችደመል | ጠጥተዋል /ለከበሬታ/ |

## <u>የማያቋርጥ ያሁን ጊዜ</u>

ይህ ከማያቋርጥ ሃላፊ ጊዜ የሚለየው ከዋነኛው ግስ ጋር ተደብሎ በሚገባው ረዳት ግስ ብቻ ነው፡፡ በዚህ የጊዜ ስርዓት ረዳት ግሱ "እምበር" (ነበር) ከመሆን ይልቅ "ኔ" ነው የሚሆነዉ. የሚከተሉትን ምሳሌዎች እንመልከት፡፡

1. ፋጢመት ወቃሊሞ እየበሌድ ኔ
   ፋጢመት ወቃሊሞ እየበላች ነዉ ፡፡
2. መሀመድ ማስ እህዱን አሸር ቤድ እያሔዲያኔ
   መሀመድ ታናሽ እህቱን ቁርአን ቤት እየወሰዳት ነዉ ፡፡
3. ኡመር እህዋ እየሽቻ ኔ
   ኡመር ዉሀ እየጠጣ ነዉ ፡፡

በዚህ የጊዜ ስርዓት ግሶች ለተለያዩ መደቦች የሚያደርጉትን እርባታ ከረዳት ግሱ ጋር አጣምረን ቀጥለን እንመልከት።

## በየማያቋርጥ ያሁን ግዜ ግሶች እርባታ

| አርጎብኛ | አማርኛ |
|---|---|
| ግስ፡ አሔዳ | ወሰደ |
| እያሔድኩ ኔ | እየወሰድኩ ነው |
| እያሔድክ ኔ | እየወሰድክ ነው |
| እያሔድች ኔ | እየወሰድሽ ነው |
| እያሔዳ ኔ | እየወሰደ ነው |
| እያሔደድ ኔ | እየወሰደች ነው |
| እያሔድን ኔ | እየወሰድን ነው |
| እያሔድኩም ኔ | እየወሰዳችሁ ነው |
| እያሔዱ ኔ | እየወሰዱ ነው |

## መሰረታዊ ቃላትና ሀረጋት

| አርጎብኛ | አማርኛ |
|---|---|
| ቀሪአ | ቀበሌ |
| ፈጫ | ወረዳ |
| ነህያ | ዞን |
| ኒቅሊም | ክልል |
| ደዉላ | መንግስት |
| ኡመት | ህዝብ |
| ፈጫ እኮኛ | ወረዳ ተመሰረተ /ተገነባ/ |
| መክተብ | ጽ/ቤት /ቢሮ/ |
| ሹራቤድ | ምክር ቤት |

| | |
|---|---|
| አርብህዶ ሀደር | አርብቶ አደር |
| አሚር ገንዳ | ጣቢያ አዛዥ |
| ሀይዋን ሲፋ ቤድ | የእንሰሳት ሀኪም ቤት |
| ሀስብ ቤድ | እስር ቤት |
| መቃሂ ቤድ | ሻይ ቤት |
| ሙስተሽፋ | ሆስፒታል |
| ፈንዱቅ | ሆቴል |
| ሲፋ ቤድ | ሀኪም ቤት |
| እህዋ ልማት | ውሃ ልማት |
| በይተል ማል | ግምጃ ቤት |
| ሂላጅ | ህክምና |
| ዊ | ፈጣሪ ጌታ /አላህ/ |
| ወዚር | ሚኒስቴር |
| ሙሉ፡ወዚር | ጠቅላይ ሚኒስትር |
| አሚር | አዛዥ |
| ሙሉ አሚር | ጠቅላይ አዛዥ |
| እሀርብ ገንዳ | የጦር ሰፈር |

| | |
|---|---|
| አጤስር | ዘውድ አገዛዝ |
| ሀርብ እፌታ | ጦር ተፈታ |
| ሀርብ ጣውራ | የጦር ዕቃ |
| ሀርብ ወዚር | የጦር ሚኒስትር |
| ሀርብ አዝማች | ጦር አዝማች |
| ሁክም | ዉሳኔ |
| እዝንጠቂ | ጆሮ ጠቢ |
| ጀዝም | ቆራጥነት |
| ጁንድ | ሠራዊት |
| ሁደድ | ድንበር |
| ኢቃብ | ቅጣት |
| ደይን | እዳ |
| አማና | አደራ |
| ሁቁቅ | መብት |
| ሱልህ | ስምምነት |
| አህድ | ቃል ኪዳን |
| መድህ | ዉደሳ |
| ነሻጣ | ሞራል |
| ሙዓሊፍ | ደራሲ |
| ገናን | ዘፋኝ |
| አባጋር | የፀሎት መሪ |
| መስናዕ | ፋብሪካ |
| መድረሳ | ትምህርት ቤት |
| አሸር ቤድ | ቁርዓን ቤት |
| ሒራሳ | ግብርና |
| ሀራስ | ገበሬ |
| ካሚዮል | መኪና |
| ሰፊና | መርከብ |

| | |
|---|---|
| ቦሊስ | ፖሊስ |
| አስከር | ወታደር |
| መቃድ ቁዋ | መብራት ኃይል |
| አውራ ሄማ | አውራ መንገድ |
| ሸንጎ | አዳራሽ |
| በርካ | በረከት |
| ከይር | በጎ |
| ሸይጣን | ሰይጣን |
| ኢብሊስ | ዲያቢሎስ |

**<u>መልመጃ</u>**

*ሀ. "ፈለገ" እና "አገኘ" የሚሉትን ግሶች በመጠቀም (ለእያንዳንዳቸው) በሁሉም የጊዜ አይነቶች አንዳንድ ዓ.ነገር ስሩ።*

*ለ. የፈለጋችሁትን ግስ በመውሰድ ከላይ በመሰረታዊ ቃላትና ሀረጋት ስር የቀረቡትን ቃላትና ሀረጋት እያስገባችሁ የተለያዩ ጊዜያትን የሚያሳዩ አ.ነገሮች ስሩ።*

## <u>ክፍል ዘጠኝ: የግሶች እርባታ - ተሳቢ አፀፋዎች</u>

አርጎብኛ ልክ እንደ አማርኛው በግስ ላይ የሚጨመሩ የባለቤት አመልካች ቅጥያ ተውላጠ ስሞች ብቻ ሳይሆን ተሳቢንና ሌሎች የዓርፍተ ነገር አካላትን የሚያመለክቱ በተለምዶ ተሳቢ አመልካች ቅጥያ ተውላጠ ስሞች የሚባሉ የተሳቢ አፀፋዎች አሉት። ባለፉት ክፍሎች ግሶች ለተለያዩ ባለቤቶች የሚያሳዩትን የባለቤት አፀፋዎች ስለተመለከትን በዚህ ክፍል የተሳቢ አፀፋዎች ላይ በተለይ ትኩረት በማድረግ በሃላፊ እና ኢሀላፊ ጊዜ ተሳቢ አፀፋዎችን ባለቤትን በመቀያየር እንመለከታለን። ሆኖም፣ አላማችን በዚህ መፅሀፍ ጥልቅ የሰዋሰው ትንታኔ ማቅረብ ሳይሆን ቋንቋውን ለማወቅ የሚረዱ ትምህርቶችን ማቅረብ ስለሆነ እነዚህን የተሳቢ አፀፋዎች ከግሶቹ ጋር በማቀናጀት ብቻ እንመለከታለን።

# ተሳቢ አፀፋዎች በሃለፊ ጊዜ

## ባለቤት: አንደኛ መደብ (እኔ)

| ግስ፡ ሀዋ | ሰጠ |
|---|---|
| ሀውኮ | ሰጠሁት |
| ሀውኳህ | ሰጠሁህ |
| ሀውኩዊህ | ሰጠሁሽ |
| ሀውኩሁሞ | ሰጠሆት |
| ሀዉኩሁም | ሰጠሁዋችሁ |
| ሀውኳ | ሰጠሁዋት |
| ሀውኮም | ሰጠሁዋቸው |
| ሀዉኮም | ሰጠሁዋቸው (አክብሮት) |

| ግስ፡ አሔደ | ወሰደ |
|---|---|
| አሔድኳህ | ወሰድኩህ |
| አሔድኩዊህ | ወሰድኩሽ |
| አሔድኩሁም | ወሰድኩዎት |
| አሔድኮ | ወሰድኩት |
| አሔድኩዋ | ወሰድኩዋት |
| አሔድኩሁም | ወሰድኩዋችሁ |
| አሔድኮም | ወሰድኩዋቸው |
| አሔድኩም | ወሰድኩዋቸው(አክብሮት) |

## ባለቤት፡ ሁለተኛ መደብ ( አንተ)

| ግስ፡ ሀዋ | ሰጠ |
|---|---|
| ሀውከኝ | ሰጠኸኝ |
| ሀውኬ | ሰጠኸው |

| | |
|---|---|
| ሀውካ | ሰጠሀት |
| ሀውክን/ሀውክና | ሰጠኸን |
| ሀውኬም | ሰጠሀቸው |
| ሀዉኬም | ሰጠሀቸው (አክብሮት) |

| | |
|---|---|
| **ግስ፡ አሔደ** | **ወሰደ** |
| አሔድከኝ | ወሰድከኝ |
| አሔድኬ | ወሰድከው |
| አሔድካ | ወሰድካት |
| አሔድኪና | ወሰድከን |
| አሔድኬም | ወሰድካቸው (ለብዙ) |
| አሔድኬም | ወሰድካቸው (አክብሮት) |

## ባለቤት፡ ሁለተኛ መደብ (አንቺ)

| | |
|---|---|
| **ግስ፡ ሀዋ** | **ሰጠ** |
| ሀውችኝ | ሰጠሽኝ |
| ሀውቺ | ሰጠሽው |
| ሀውቻ | ሰጠሻት |
| ሀውችን/ሀውችና | ሀጠሽን |
| ሀውቼም | ሰጠሻቸው |
| ሀዉቼም | ሰጠሻቸው (አክብሮት) |

| | |
|---|---|
| **ግስ፡ አሔዳ** | **ወሰደ** |
| አሔድችኝ | ወሰድሽኝ |
| አሔድቺ | ወሰድሽው |
| አሔድቻ | ወሰድሻት |
| አሔድቺን | ወሰድሽን |

| | |
|---|---|
| አሔድቼም | ወሰድሻቸው ( ለብዙ) |
| አሔድኬም | ወሰድካቸው (አክብሮት) |

*ባለቤት ሁለተኛ መደብ አክብሮት (እርስዎ/ አንቱ)*

| | |
|---|---|
| ሀውኝ | ሰጡኝ |
| ሀዊ | ሰጡት |
| ሀዉዋ | ሰጧት |
| ሀውን | ሰጡን |
| ሀዉዎም | ሰጡዋቸው (ለብዙ) |
| ሀዉዎም | ሰጡዋቸው (አክብሮት) |

| | |
|---|---|
| ግስ፡ አሔዳ | ወሰደ |
| አሔዱኝ | ወሰዱኝ |
| አሔዲ | ወሰዱት |
| አሔዱዋ | ወሰዱዋት |
| አሔዱና | ወሰዱን |
| አሔዶም | ወሰዱዋቸው |
| አሔዶም | ወሰዱዋቸው (አክብሮት) |

**ባለቤት፡ ሶስተኛ መደብ (እሱ)**

| | |
|---|---|
| ግስ፡ ሀዋ | ሰጠ |
| ሀወኝ | ሰጠኝ |
| ሀዋሀ | ሰጠሀ |
| ሀዊሀ | ሰጠሽ |
| ሀዉሁም | ሰጠዎት |
| ሀዉዌ | ሰጠው |

| | |
|---|---|
| ሀዋ | ሰጣት |
| ሀወን/ሀወና | ሰጠን |
| ሀውኩም | ሰጣችሁ |
| ሀዌም | ሰጣቸው (ለብዙ) |
| ሀዌም | ሰጣቸው (አክብሮት) |

| | |
|---|---|
| ግስ፡ አሔዳ | ወሰደ |
| አሔደኝ | ወሰደኝ |
| አሔዳህ | ወሰደህ |
| አሔዲህ | ወሰደሽ |
| አሔዱሁም | ወሰደዎት |
| አሔዴ | ወሰደው |
| አሔዳ/አሔዲያ | ወሰዳት |
| አሔደን | ወሰደን |
| አሔዱሁም | ወሰዳችሁ |
| አሔዴም | ወሰዳቸው |
| አሔዴም | ወስዳቸው (አክብሮት) |

## ባለቤት፡ ሶስተኛ መደብ (እሷ)

| | |
|---|---|
| ግስ፡ ሀዋ | ሰጠ |
| ሀወተኝ | ሰጠችኝ |
| ሀወታህ | ሰጠችህ |
| ሀወቲህ | ሰጠችሽ |
| ሀወቱሁም | ሰጠችዎት |
| ሀወታ | ሰጠቻት |
| ሀወቴ | ሰጠችው |

| | |
|---|---|
| ሀወተና | ሰጠችን |
| ሀወቱሁም | ሰጠቻችሁ |
| ሀወቴም | ሰጠቻቸው |
| ሀወቴም | ሰጠቻቸው(አክብሮት) |

| | |
|---|---|
| ግስ፡ አሔዳ | ወሰደ |
| አሔደተኝ | ወሰደችኝ |
| አሔደታህ | ወሰደችሕ |
| አሔደቲህ | ወሰደችሽ |
| አሔደቱሁም | ወሰደችዎት |
| አሔደታ | ወሰደቻት |
| አሔደቴ | ወሰደችው |
| አሔደተና | ወሰደችን |
| አሔደቱሁም | ወሰደቻችሁ |
| አሔደቴም | ወሰደቻቸው |
| አሔደቴም | ወሰደቻቸው (አክብሮት) |

## ባለቤት አንደኛ መደብ (እኛ)

| | |
|---|---|
| ግስ፡ ሀዋ | ሰጠ |
| ሀውናህ | ሰጠንህ |
| ሀውኒህ | ሰጠንሽ |
| ሀውኑሁም | ሰጠንዎት |
| ሀውኔ | ሰጠነው |
| ሀውና | ሰጠናት |
| ሀውኑሁም | ሰጠናችሁ |
| ሀውኔም | ሰጠናቸው |
| ሀዉኔም | ሰጠናቸው (አክብሮት) |

ግስ፡ አሔዳ	ወሰደ

| | |
|---|---|
| ግስ፡ አሔዳ | ወሰደ |
| አሔድናህ | ወሰድንህ |
| አሔድኒህ | ወሰድንሽ |
| አሔድኑሁም | ወሰድንዎት |
| አሔድኔ | ወሰድነው |
| አሔድና | ወሰድናት |
| አሔድኔም | ወሰድናችዉ |
| አሔድኑሁም | ወሰድናችሁ |
| አሔድኔም | ወሰድናቸው (አክብሮት) |

## ባለቤት፡ ሁለተኛ መደብ (እናንተ)

| | |
|---|---|
| ግስ፡ ሀዋ | ሰጠ |
| ሀዉኩሚኝ | ሰጣችሁኝ |
| ሀውኩሚ | ሰጣችሁት |
| ሀውኩማ | ሰጣችኋት |
| ሀውኩምና | ሰጣችሁን |
| ሀውኩሜም | ሰጣችኋቸው |
| ሀ ሀዉኩሜሞ | ሰጣችኋቸው (አክብሮት) |
| ግስ፡ አሔዳ | ወሰደ |
| አሔድኩምኝ | ወሰዳችሁኝ |
| አሔድኩሚ | ወሰዳችሁት |
| አሒድኩማ | ወሰዳችኋት |
| አሔድኩምና | ወሰዳችሁን |
| አሔድኩማዉ | ወሰዳችኋቸው |
| አሔድኩማዉ | ወሰዳችኋቸው (አክብሮት) |

## ባለቤት ሶስተኛ መደብ (እነርሱ)

| | |
|---|---|
| ግስ፡ ሀዋ | ሰጠ |
| ሀውኝ | ሰጡኝ |
| ሀውክ | ሰጡህ |
| ሀውች | ሰጡሽ |
| ሀውኩም | ሰጡዎት |
| ሀዊ | ሰጡት |
| ሀዉዋ | ሰጧት |
| ሀውዋ | ሰጡን |
| ሀውኩም | ሰጡዋችሁ |
| ሀዉዎም | ሰጡዋቸው |
| ሀዉዎም | ሰጡዋቸው (አክብሮት) |

| | |
|---|---|
| ግስ፡ አሔዳ | ወሰደ |
| አሔዱኝ | ወሰዱኝ |
| አሔዱክ | ወሰዱህ |
| አሔዱች | ወሰዱሽ |
| አሔዱኩም | ወሰዱዎት |
| አሔዲ | ወሰዱት |
| አሔዱዋ | ወሰዱዋት |
| አሔዱኛ | ወሰዱን |
| አሔዱሁም/ አሔዱኩም | ወሰዱዋችሁ |
| አሔዶም | ወሰዱዋቸው |
| አሔዶም | ወሰዱዋቸው (አክብሮት) |

## <u>ባለቤት ሶስተኛ መደብ አክብሮት (እሳቸው)</u>

የሶስተኛ መደብ አክብሮት ከሶስተኛ መደብ ብዙ ቁጥር ጋር እርባታው አንድ ነው። ለዚህም በሶስተኛ መደብ ብዙ ቁጥር የቀረበውን በዚህ ስር ከተዘረዘረው ጋር በማነፃፀር ይመልከቱ።

| | |
|---|---|
| ግስ፡ ሀዋ | ሰጠ |
| ሀውኝ | ሰጡኝ |
| ሀውክ | ሰጡህ |
| ሀውች | ሰጡሽ |
| ሀውኩም | ሰጡዎት |
| ሀዊ | ሰጡት |
| ሀዊያ | ሰጧት |
| ሀውዋ | ሰጡን |
| ሀውኩም | ሰጡዋችሁ |
| ሀዉዎም | ሰጡዋቸው |
| ሀዎም | ሰጡዋቸው (አክብሮት) |

| | |
|---|---|
| ግስ፡ አሔዳ | ወሰደ |
| አሔዱኝ | ወሰዱኝ |
| አሔዱክ | ወሰዱህ |
| አሔዱች | ወሰዱሽ |
| አሔዱኩም | ወሰዱዎት |
| አሔዲ | ወሰዱት |
| አሔዱዋ | ወሰዱዋት |
| አሔዱና | ወሰዱን |
| አሔዱሁም/ አሔዱኩም | ወሰዱዋችሁ |

አሔዶም ወሰዱዋቸው

አሔዶም ወሰዱዋቸው (አክብሮት)

## ማብራሪያ

ከላይ በእርባታዎቹ ላይ እንደተመለከትነው በሁለቱም መደቦች (ሁለተኛና ሶስተኛ መደቦች) ያለው የአክብሮት እርባታ ከሶስተኛ መደብ ብዙ ቁጥር ጋር አንድ ነው። ይህ ልክ እንደ አማርኛው ማለት ነው። ግሱ በኢሀላፊ ቅርጽ በሚሆንበትም ወቅት በአክብሮት የሚታየው አፀፋ ልክ እንደሃለፊው ጊዜ ከሶስተኛው መደብ ብዙ ቁጥር ጋር አንድ ነው።

<u>መልመጃ</u>

ሀ. የሚከተሉትን ዓ.ነገሮች ወደ አርጎብኛ ተርጉሟቸው።

አቶ ኡመር ቤታቸውን ሸጡት።

መሪም አንሻን ተጣላቻት።

(አንቺ) መፅሀፉን ወሰድሽው።

ሀሰን እኛን ወደ ትምህርት ቤት ወሰደን።

አንሻ መፅሀፉን ሰጠችኝ።

ለ. የሚከተሉትን ዓ.ነገሮች ወደ አማርኛ ተርጉሟቸው።

1. ሱቻቹ ጣዉራሙን አሔዱ
2. አንሻ ኪታቡን ሊምሚ ሀወታ
3. መሀመድ ዘዉጂቱን መድረሳ ቤድ አሔድ
4. ለፋጢመት ሜራቿቀርሽ ሀዉዋ
5. እህዬ መካቻ ሀዉወኝ

መ. "ፈለገ"፣ "ሰበረ" እና "ወደደ" የሚሉትን ግሶች በመጠቀም ባለቤታቸውን ወይም ተሳቢያቸውን በመቀያየር በእያንዳንዳቸው ሶስት ሶስት ዓ.ነገር ስሩ።

ምሳሌ፡- 1. ኡመር ብርጭቆውን ሰበረው።

እኛ ብርጭቆውን ሰበርነው።

እኔ ብርጭቆውን ሰበርኩት።

## የኢሀላፊ ግስ የተሳቢ አፀፋዎች እርባታ

### ባለቤት አንደኛ መደብ (እኔ)

| ግስ፡ ሀዋ | ሰጠ |
|---|---|
| አሀዋሀሉህ | እሰጥሀለሁ |
| አሀዊኽሉህ | እሰጥሻለሁ |
| አሀውሁመሉህ | እሰጥዎታለሁ |
| አሀዌሉህ | እሰጠዋለሁ |
| አሀዋሉህ | እሰጣታለሁ |
| አሀውሁመሉህ | እሰጣችኋለሁ |
| አሀዌመሉህ | እሰጣቸዋለሁ |
| አሀዌ መሉህ | እሰጣቸዋለሁ (አክብሮት) |

| ግስ፡ አሔደ | ወሰደ |
|---|---|
| አሔዳሀሉህ | እወስድሀለሁ |
| አሔዲክሉህ | እወስድሻለሁ |
| አሔዱሁመሉህ | እወስድዎታለሁ |
| አሔዴሉህ | እወስደዋለሁ |
| አሔዳሉህ | እወስዳታለሁ |
| አሔዱሁመሉህ | እወስዳችኋለሁ |
| አሔዴመሉህ | እወስዳቸዋለሁ |
| አሔዴ መሉህ | እወስዳቸዋለሁ (አክብሮት) |

### ባለቤት፡ ሁለተኛ መደብ (አንተ)

| | |
|---|---|
| ግስ፡ ሀዋ | ሰጠ |
| ታሀወኘላህ | ትሰጠኛለህ |
| ታሀዌላህ | ትሰጠዋለህ |
| ታሀዋላህ | ትሰጣታለህ |
| ታሀወነላህ | ትሰጠናለህ |
| ታሀዌመላህ | ትሰጣቸዋለህ |
| ታሀዌ መላህ | ትሰጣቸዋለህ (አክብሮት) |
| ግስ፡ አሔዳ | ወሰደ |
| ታሔደኘላህ | ትወስደኛለህ |
| ታሔዴላህ | ትወስደዋለህ |
| ታሔዳላህ | ትወስዳታለህ |
| ታሔደነላህ | ትወስደናለህ |
| ታሔዴመለህ | ትወስዳቸዋለህ |
| ታሔዴመላህ | ትወስዳቸዋለህ (አክብሮት) |

## ባለቤት፡ ሁለተኛ መደብ (አንቺ)

| | |
|---|---|
| ግስ፡ ሀዋ | ሰጠ |
| ታሀዊኘሊህ | ትሰጭኛለሽ |
| ታሀዊለህ | ትሰጭዋለሽ |
| ታሀዊያሊህ | ትሰጫታለሽ |
| ታሀዊነሊህ | ትሰጭናለሽ |
| ታሀዌ መሊህ | ትሰጫቸዋለሽ |
| ታሀዌ መሊህ | ትሰጫቸዋለሽ (አክብሮት) |
| ግስ፡ አሔዳ | ወሰደ |
| ታሔጂፐሊህ | ትወስጅኛለሽ |

| | |
|---|---|
| ታሔጂሊህ | ትወስጅዋለሽ |
| ታሔጃሊህ | ትወስጃታለሽ |
| ታሔጂነሊህ | ትወስጅናለሽ |
| ታሔጆመሊህ | ትወስጃቸዋለሽ |
| ታሔጆመሊህ | ትወስጃቸዋለሽ (አክብሮት) |

## ባለቤት ሁለተኛ መደብ አክብሮት (እርስዎ/ አንቱ)

| | |
|---|---|
| ግስ፡ ሀዋ | ሰጠ |
| ያሀውኘል | ይሰጡኛል |
| ያሀዊል | ይሰጡታል |
| ያሀዊያል | ይሰጧታል |
| ያሀውነል | ይሰጡናል |
| ያሀዎመል | ይሰጡዋቸዋል |
| ያሀዎመል | ይሰጡዋቸዋል (አክብሮት) |

| | |
|---|---|
| ግስ፡አሔዳ | ወሰደ |
| ያሔዱኘል | ይወስዱኘል |
| ያሔዱኩመል | ይወስዱዎታል |
| ያሔዲል | ይወስዱታል |
| ያሔዱዋል | ይወስዷታል |
| ያሔዱናል | ይወስዱናል |
| ያሔዶመል | ይወስዱዋቸዋል |
| ያሔዶመል | ይወስዱኛል (አክብሮት) |

## ባለቤት፡ ሶስተኛ መደብ (እሱ)

| | |
|---|---|
| ግስ፡ ሀዋ | ሰጠ |
| ያሀወኝል | ይሰጠኛ ል |
| ያሀዋሀል | ይሰጥሀል |
| ያሀዊኽል | ይሰጥሻል |
| ያሀውሁመል | ይሰጥዎታል |
| ያሀዌል | ይሰጠዋል |
| ያሀዊያል | ይሰጣታል |
| ያሀወነል | ይሰጠናል |
| ያሀውሁመል | ይሰጣችኊል |
| ያሀዌመል | ይሰጣቸዋል |
| ያሀዌመል | ይሰጣቸዋል (አክብሮት) |

| | |
|---|---|
| ግስ፡ አሔዳ | ወሰደ |
| ያሔደኝል | ይወስደኝል |
| ያሔድከል | ይወስድሀል |
| ያሔድኽል | ይወስድሻል |
| ያሔደዱሁመል | ይወስድዎታል |
| ያሔዴል | ይወስደዋል |
| ያሔዲያል | ይወስዳታል |
| ያሔደናል | ይወስደናል |
| ያሔዱሁመል | ይወስዳችኊል |
| ያሔዴመል | ይወስዳቸዋል |
| ያሔዴመል | ይወስዳቸዋል (አክብሮት) |

## ባለቤት፡ ሶስተኛ መደብ (እሷ)

ግስ፡ ሀዋ ሰጠ

| | |
|---|---|
| ታሀወኘለድ | ትሰጠኛለች |
| ታሀዋሀለድ | ትሰጥሀለች |
| ታሀዊኸለድ | ትሰጥሻለች |
| ታሀውሁመለድ | ትሰጥዎታለች |
| ታሀዌለድ | ትሰጠዋለች |
| ታሀወለድ | ትሰጣታለች |
| ታሀወናለድ | ትሰጠናለች |
| ታሀውሁመለድ | ትሰጣችኂለች |
| ታሀዎመለድ | ትሰጣቸዋለች |
| ታሀዌመለድ | ትሰጣቸዋለች (አክብሮት) |

| | |
|---|---|
| **ግስ፡ አሔዳ** | **ወሰደ** |
| ታሔደኘለድ | ትወስደኛለች |
| ታሔዳሀለድ | ትወስድሀለች |
| ታሔዲኸለድ | ትወስድሻለች |
| ታሔዱሁመለድ | ትወስድዎታለች |
| ታሔዴለድ | ትወስደዋለች |
| ታሔዳለድ | ትወስዳታለች |
| ታሔደነለድ | ትወስደናለች |
| ታሔዱሁመለድ | ትወስዳችኂለች |
| ታሔዴመለድ | ትወስዳቸዋለች |
| ታሔዴመለድ | ትወስዳቸዋለች (አክብሮት) |

**ባለቤት፡ አንደኛ መደብ (እኛ)**

| | |
|---|---|
| **ግስ፡ ሀዋ** | **ሰጠ** |
| እናሀውክልን | እንሰጥሀለን |

| | |
|---|---|
| እናሀዊኽልን | እንሰጥሻለን |
| እናሀውኩመልን | እንሰጥዎታለን |
| እናሀዌልን | እንሰጠዋለን |
| እንሀዋልን | እንሰጣታለን |
| እናሀውሁመልን | እንሰጣችኋለን |
| እናሀዌመልን | እንሰጣቸዋለን |
| እናሀዌመልን | እንሰጣቸዋለን (አክብሮት) |

| ግስ፡ አሔዳ | ወሰደ |
|---|---|
| እናሔዳሀልን | እንወስድሀለን |
| እናሔዲኽልን | እንወስድሻለን |
| እናሔዱሁመልን | እንወስድዎታለን |
| እናሔዴልን | እንወስደዋለን |
| እናሔዳልን | እንወስዳታለን |
| እናሔዱሁመልን | እንወስዳችኋለን |
| እናሔዱሁመልን | እንወስዳችኋለን |
| እናሔዴመልን | እንወስዳቸዋለን (አክብሮት) |

## ባለቤት፡ ሁለተኛ መደብ (እናንተ)

| ግስ፡ ሀዋ | ሰጠ |
|---|---|
| ታሀዉኘሉሁም | ትሰጡኛላችሁ |
| ታሀዊሉሁም | ትሰጡታላችሁ |
| ታሀዋሉሁም | ትሰጧታላችሁ |
| ታሀውነሉሁም | ትሰጡናላችሁ |
| ታሀዎመሉሁም | ትሰጧቸዋላችሁ |
| ታሀዎመሉሁም | ትሰጧቸዋላችሁ (አክብሮት) |

| | |
|---|---|
| ግስ፡ አሔዳ | ወሰደ |
| ታሔዱኝሉሁም | ትወስዱኛላችሁ |
| ታሔዲሊሁም | ትወስዱታላችሁ |
| ታሔዷሉሁም | ትወስዱዋታላችሁ |
| ታሔዱነሉሁም | ትወስዱናላችሁ |
| ታሔዶመሉሁም | ትወስዱዋቸዋላችሁ |
| ታሔዶዎመሉሁም | ትወስዱዋቸዋላችሁ (አክብሮት) |

## ባለቤት ሶስተኛ መደብ (እነርሱ)

| | |
|---|---|
| ግስ፡ ሀዋ | ሰጠ |
| ያሀውኝል | ይሰጡኛል |
| ያሀውክል | ይሰጡሀል |
| ያሀውችል | ይሰጡሻል |
| ያሀውኩመል | ይሰጠዎታል |
| ያሀዊል | ይሰጡታል |
| ያሀዊያል | ይሰጧታል |
| ያሀውነል | ይሰጡናል |
| ያሀውኩመል | ይሰጡዋችኋል |
| ያሀዎመል | ይሰጡዋቸዋል |
| ያህዎመል | ይሰጡዋቸዋል (አክብሮት) |

| | |
|---|---|
| ግስ፡አሔዳ | ወሰደ |
| ያሔዱኝል | ይወስዱኛል |
| ያሔዱክል | ይወስዱሀል |
| ያሔዱችል | ይወስዱሻል |
| ያሔዱኩመል | ይወስዱዎታል |

| | |
|---|---|
| ያሔዲል | ይወስዱታል |
| ያሔዱዋል | ይወስዷታል |
| ያሔዱናል | ይወስዱናል |
| ያሔዱኩመል | ይወስዷችኋል |
| ያሔዶመል | ይወስዱዋቸዋል |
| ያሔዱኝል | ይወስዱኛል (አክብሮት) |

## ባለቤት ሶስተኛ መደብ አክብሮት (እሳቸው)

ከላይ እንደተገለፀው ለአክብሮት ያለው የግስ እርባታ ልክ እንደ ሶስተኛው መደብ ብዙ ቁጥር ነው። የሚከተለውን በብዙ ቁጥር ስር ካለው ጋር በንፅፅር ይመልከቱ።

| ግስ፡ ሀዋ | ሰጠ |
|---|---|
| ያሀውኝል | ይሰጡኛል |
| ያሀውከል | ይሰጡሀል |
| ያሀውቸል | ይሰጡሻል |
| ያሀውኩመል | ይሰጠዎታል |
| ያሀዊል | ይሰጡታል |
| ያሀዊያል | ይሰጧታል |
| ያሀውነል | ይሰጡናል |
| ያሀውኩመል | ይሰጡዋችኋል |
| ያሀዎመል | ይሰጡዋቸዋል |
| ያሀዎመል | ይሰጡዋቸዋል (አክብሮት) |

| ግስ፡አሔዳ | ወሰደ |
|---|---|
| ያሔዱኝል | ይወስዱኛል |
| ያሔዱከል | ይወስዱሀል |

| | |
|---|---|
| ያሔዱቸል | ይወስዱሻል |
| ያሔዱሁመል | ይወስዱዎታል |
| ያሔዲል | ይወስዱታል |
| ያሔዱዋል | ይወስዷታል |
| ያሔዱነል | ይወስዱናል |
| ያሔዱኩመል | ይወስዷችኂል |
| ያሔዶመል | ይወስዱዋቸዋል |
| ያሔዱኘል | ይወስዱኛል (አክብሮት) |

<u>መልመጃ</u>

ሀ. የሚከተሉትን ዓ.ነገሮች ወደ አርጎብኛ ተርጉሟቸው፡፡

አቶ ኡመር ቤታቸውን ይሸጡታል፡፡

መሬም አንሻን ትታረቃታለች፡፡

(አንቺ) መፅሀፉን ትወሰጅዋለሽ፡፡

ሀሰን እኛን ወደ ትምህርት ቤት ይወሰደናል፡፡

አንሻ መፅሀፉን ትሰጠኝአለች፡፡

ለ. የሚከተሉትን ዓ.ነገሮች ወደ አማርኛ ተርጉሟቸው፡፡

1. ልጋቾቸን ጉሳ አሐዴ መሉህ
2. መሀመድ ረፊቁን አልዩ ጌ ያሔዴል
3. እይ/ኦን በዘር አሔዱሁመሉህ
4. ነግ ሚሴን አስከራች ቀጥርደሚል
5. አንሻ በመቀነቷየዋዘቴን ቀርሽ ሻሪቅ አሔደባ

መ. “ፈለገ”፣ “ሰበረ” እና “ወደደ” የሚሉትን ግሶች በመጠቀም ባለቤታቸውን ወይም ተሳቢያቸውን በመቀያየር በእያንዳንዳቸው ሶስት ሶስት ዓ.ነገር ስሩ፡፡

ምሳሌ፡- 1. ኡመር ብርጭቆውን ይሰብረዋል።
እኛ ብርጭቆውን እንሰብረዋለን።
እኔ ብርጭቆውን እሰብረዋለሁ።

**አጋዥ ፅሁፎች**

Leslau, Wolf. 1997. *Ethiopic Documents – Argobba: Grammar and Dictionary*. Wiesbaden: Harrassowitz Verlag.

# ምስጋና

ይህ የአርጎብኛ ቋንቋ መማሪያ መለስተኛ መጽሀፍ ለማዘጋጀት ከጥናት ጀምሮ እስከ ህትመት ድረስ ባለዉ ሒደት የተለያዩ ድጋፍና ትብብር ላደረጉልን ሁሉ ልባዊ ምስጋናችንን እያቀረብን ለሚከተሉት አካላት የተለየ ምስጋና ማቅረብ እንወዳለን ።

**ድርጅቶች**

- የአርጎባ ልማት ማህበር
- የአርጎባ ብሄረሰብ ልዩ ወረዳ /ጋቸኔ/
- በአዲስ አበባ ዩኒቨርስቲ የቋንቋዎች ጥናት ማዕከል ኢንስቲትዩት

<u>ግለሰቦች</u>

- አቶ ሰይድ ይመር (የአርጎባ ልማት ማህበር ስራ አስኪያጅ )
- አቶ አብዱል ቃድር መሀመድ (አቦ)
- ፕሮፌሰር መሀመድ ሀቢብ (የአዲስ አበባ ዩኒቨርስቲ ..... )
- ሀጅ አህመድ በሽርእብራሂም የብራዘርስ ብስኩትና ዱቄት ፋብሪካ ባለቤት
- መሀመድ አሚን እብራሂም
- መሀመድ አቡበከር
- መሀመድ ሳሊህ
- ዙሪያሽ አሊ እና ቤቲ አህመድ ይህን ጽሁፍ በጥንቃቄ በኮምፒዉተር በተደጋጋሚ በማረምና በመጻፍ

# <u>በአርጎብኛ ቋንቋ የቀረበ ግጥም</u>

በጠፋዉ አርጎባ በሀላዉ ብትንትን

ሀንድ ሀንድ ሡ አይጠፉ በጌሙ ብልሄድን

እስቲ ልሀንግኔ ቀይሕ ባህርን ዊደን

ብሌን ራሻይዳ ቢኒ አምር ብልደን

ጅቡቲ ተጆራ አዉሳ ከቢርቶን

ትግራይ አዶ ከቢር ወሎ አናሄደን

በወረሂበኖ ጎንደር ጎጃም ዞርደን

በየጁ በላሌ ወረባቡ ብልደን
በባቲ በደጋን በገርባ መኝደን
ብዙ ሡቻች ሀሉ አፈሙን ለዉጥደም
ሌላ አፍ ይዋዥሉ የነብሰሙን ጢልደም
ሡነተሙ ቢሆን ዎዱ አርጎባ ኤም
እሸጥ እልፍ ብልደን ወሌ ብልሀንጅኔ
ከሜ ከሜን ጢልደም ይለሉ ድማኔ
ሀንድ ሀነዱ ዉዥዙ ቲና መስ ግጥምኔ
ቢሆንም ተቀራዉ የክሠም ወገርኔ
አዳሙ ላኪን ሲሀንጅ ብዙሀኔ
ኦሮምኛም ቢዋዥ አርጎባ አርጎባኔ
ተወድ እነስደን ስልገብን በግድም
አርጎባቹ ሀሉ ያማራ አፍ ዊደም
አፈሙ ቀራ እንጅ ሱቻቸ አልጠፉም
ሁድንስ ሀንጀኔ ወሌ ይፋት ልግብን
የጎዜን አዉሊያ ዚያራ መኝደን
አዉሁሴን ፈቂህ አህመድ ወሊ ሙሀመድን
ሸህ አንበሥ ጥንኩቼ የቅጧባቹን
ወላኪን የፋት ጌ ተቀራዉ ይሺለል
አዳና ዉዥዢዉ እሸጥ እሸጥ ይለል
በመህፍዝ መኝደን አሊንግብ በሌፍ
ጨኖ በሚሊግ ገቤን ሳንሀርፍ
አዉሊያ ኡለማ ድዩም ቢንበረቦ
ጡሉሉን ሲሀንጅ ሱሃባም ሀለቦ

ሀፊዘል ቁርአንም ብዙህ ሀንጀቦ

የሰኺይ የተቂይ ጌዉ ጨኖ እምበር

ከምሆናና ቀራ ዱንያ ሲሀልቅ አያምር

የኒስቻዉን ምጥን አረብ ያወደሴ

የሄዳዉን አረብ ተጌዉ የመሌሴ

ኸበረሙን ቢሰም ቀልቡን አላወሴ

እልባ ሲመጥ በጌዉ ድዮም ይ3ሻሙ እምበር

አይ ግን አይ ግን ሲሉ ይሳኑ እምበር

ገላጋይ ይገበል ስልስምን ኸበር

ኸበሩ አይሀልቁ በሀጭሩ ይቅር

ተጌዉ ሁላ በፊድ የሰለጠና እምበር

ተጨኖ አልዩጌ ስለልክ ይማማጡ እምበር

ደብረኮም የሚሉ ክሱም ለሀም ጌምበር

የዋደሙ ስፋት አዋሽ ይገብ እምበር

ተክሱ ቀጥልዶ አርቧ አይገብር ይሊል

ተብርዬ ታማራ ሌፍ ሌፍን በኩል

ተሰባ ቆራሬ ወደ ቂብላ ሲል

በሰባ ቆራሬ በኢልሙ መዲና

አሊም ይሆን እምበር ቢሙ ይቀርና

አሊም ይሆን እምበር ባዉ ይቀርና

አይሄዱም በሠፈር መቼ ጋር ሀጡና

ፈኑን ይጨርሲል ቤድ ይሆኑና

ዋዱንም ይሀርሲል ጦለብ የላዉ ቢና

ጋሩንም ሲግሪ እንደ ኢልመሙኔ

አይከጅሉም ተሡ ድዮም ከለብዶኔ

ቁርአኑን ሀዲሱን ሰያመጢ ሀፍዝደም

ተንቢህ አብዱል ጀሊል ደላኢል ጨምርደም

ወሌ ታመጢ ጄድ ቢንጀሙ ከትብደም

ለሙሊ ሀበሻ ያበዚ ክሰም ኔም

አስሩን ሙጀለድ የቱህፋን ኪታብ

ሀፍዝደም አመጢ ጎድኔ የሚአጅብ

ወሌ ሁድን ሙሊ በኒሽታ እንጅ መክተብ

አንበይ በሀበሻየላዉ በአረብ

የኪታብ ሙሊ አሰል ዎዱ ቆራሬኔ

የክሰም ወርጅናል የቀራዉ ቅጂኔ

ላሀም ላሀም ሱቻች ስልሰምን ኸበር

በጌዉ ሌፍ ሲሀልፍ ጫማ ያወልቁ እምበር

ለጌዉ ሁርማ ሲሉ የሚወንቁ ቀድር

ኒስቻዉ እየፈጫ አልፈያን ይቀረል

ወንዱ ተህርሻዉ መስ ኪታብ ይሀፍዛል

ሀንድ ፈር አወጥዶ ኪታቡን ይሀንጄል

ይሀንጄል ሲሀፍዝ ብዙህ ጋር ይጊራል

የቆራሬ ኸበር በሁዱ ይበቀል

ተዳሩ በአደብ መመለስ ይሺለል

ቴፉም መጠቅለያ ተሁዱ መስኔ

ሌፉም መጠቅለያ ክሡም ተሁዱኔ

መጠቅለያ ያሊ ያሀኝ የጄድ ስምኔ

የድዮም መጠሪያዉ ሰባ ቆራሬኔ

አልዩጌም ሳይቀር ተሰባዉ መስኔ
የጉምሩኩ ቀረጥ መጀመሪያ ያልኔ
ተሁድ በተረፈ ዘጠና ዲቢኔ
የምራሁ ካርታ እንዳሀኙም አህኔ
ወሌ በበረኸት ሄደን ብልሀንጅኔ
ስመሙ የወጤ በሸጃእነትኔ
ከሠምን የሚነክ ከሜ የሀላሱኔ
ከነኬምም በጄድ ማደሩ ክስትኔ
ከነብር መሳኒድ የማይቀደርኄ
በሌ በለ ብልደም ሲምጢ ክራሩን
አንበይ የሱዉን ልጅ ይነሸጤልነብሩን
ክስቴንም ተሆና ጠይቀ ኸበሩን
ብየሁሉም ቢሉ ክሡም ይናዉጌኔ
ጨርጨርም የሚሉ ብዙሁ አርጎባኔ
ኦሮሞ ቢበዝህም ቲናዉ መስ ሆንዶኔ
ይናዉ ዘሪች ኔም በባሌም ብልሄድን
አርጎባች ሙሊ አዉ ሠይደል አረፊን
በሁድም አያበቅ ይገበልሀረርጌ
በአሚር አብደሏህ በነሠእነደዲንጌ
ስላዉዣዢምኔም አማን ተሁ ሀሉን
የአርጎባ ነገር ዎዱኔ ምራሁን
ያዉን እየተዋ ሌላ መዋዢዱን
ኮዱን ይለዉጤል ያመጤል ሀግሡን
ከምከም እየሀላኔ ያሀላፌ ቀናዉን

የላዉ እሰተሚሉ ቴዉዶ መዋዢዱን
አሀኝ ሊዋዝኔ አግኝዶል ሁሩን
ላኪን ብዙሁን ቃል አማራ አሂዶየል
እስኪ ልሰብስብኔ የጌኛዉን ያህል
የአረብን ዉዥዡ አርጎባ ሳሪቅኔ
አማራ አቀብዶ መወዠዠ መኜ
ቢንጀሙም ጌኛ ላሀም ቂም ነገርኔ
በሁድ አትቆጡ መዋዢድ ሀቂንኔ
ዉዢዢኛ ባይሆን አዉና ልጋችኔ
አሊም ልጠይቅን አዎ የድኛዉ ኔ
ያርጎባን ዉዥዡ ስብስብደን ከትብደን
የዛፍ ስም ስልጠርህን ሁድ ይናኔ ሀሉን
መዛዚ ቀጥቀጬ ሰምያ ቂናቂራ
ቢናኔ ኔ እንግ የላዉ በአምሀራ
ባማራ ዉዥዠ አረብ ጥቅሳ ጥቅሱ
እና ገርምደኔ ክሡምም ዌረሱ
ይናኔ ይለሉ በማን ይዌቀሱ
ሊበሊያ ያሀሰቢያን ደሮ ጅግራ እንደሚሊ
አርጎባች ጠፍደመል ይለል ባፉ ሙሊ
ለማን ሊመኝኔ ይፋትን በሙሊ
ብዙህ እልፍ ቃልና ብዙህ ቀያይህሡ
 በክሰም ግን ሀሉ ቲና የዌረሱ
በሕግ ሽምግልና በሽሪአም አህኔ
ቲና የወረሶም ከሙን በከይድኔ

በተረፈና ቃል ልንወዣዥኔ

አናሳ አትበሉና ስምኖ ላሀምኔ

ላሀምን ማሳነስ በጌኖ አይብኔ

ርቢሁም ቢኬፈል ብዙህ ይኼንጅ እምበር

አናሳ ይለሉ የማይወንቂ ነገር

ተሙሰዋእ ዊዶ ዘይላእ ሱማል ምድር

ጌዉን ስላቅንኔ ቲና መስ ማን እምበር

አማራ ተቁንዲ ወርዶ የወንቅ እምበር?

ጭራሽአልሴማዉ ከም የሀላ ኸበር

በቆላ ምድር ሌፍ ወባ ይፈር እምበር

በሱማሌም ምድር ዘረችኖን ሀንጄን

ሱማኢል ለበርቲ የሚሎም ስመሙን

አፈሙ ጤፈና እንዳላዋዥኔም

ወሊ ስንሀንጅ በአፋር ሴካ ሴካ እሚሊም

በጄድ ቢለያይም ታርጎባ አፈርን

አልቆራረጣዉሲሊቲ ረሂሙን

በሀንድ መስ ሆንዶል ደዉላሙ ጭራሹን

እለያይዶም አይወንቅ አርጎባና አፈር

በዲጊብ ማቀባይ በመዉሊድ በቀብር

ባንዶይታ በሰግደት በዱአም ሳይቀር

ታርጎባ መስኔ ሙላዉም ሲዴበር

ሲና ይሳኑና እምበይ ሡ ቢሞዴም

ቀብሩን ይመኙሉ ኬቱም ባንድ ሆንደም

ታእዚያም ይመኻሉ በሀንድ እሰብሰብደም
ገበያሙም አይቀር በሀንድ ይዉለሉ
ፖሊስም ልዝግ ቢል ጢልደም ይመጠሉ
እለያይዶ መኖር መቸ ይወቀሉ
በአዘሎም ጂሀት ብዙሀ አርጎባ እምበር
ወይ ጭራሽ ሀልቅዶል ወይም ሆንዶል አፈር
ዳጎ ብንመኛኝ እናገኜም እምበር
ዘሪኖ ቴርፍዶ ለሙሊ ሀበሻ
ዉዥዠኖ ቴርፍዶ ለመሊ ሀበሻ
በነብሰኖ ምድር ከሜ ልሀጥን ድርሻ
ወደ ሌፍ ብልወጥን ያዉኖ ጡሉልኔ
ወደ ቴፍ ብልወርድን ያዉኖ ጡሉልኔ
ሁድ እምር የቀራም ኢሀአዲግ ባይሰምኔ
ዊዝዶ የመጤ ሁቁቅ ለድዮም ሀንድኔ
ያጤዎችን ዘመን አኗሀ አሴልፍዶን
በኢሀአዲግ ዘመን ወሌ ታዴረሰን
ዲሞክራሲ ሆንዶ ተቀራ መጫጫን
ለመለስ ዜናዊ ዱአ እየመኘን
ምራሀ ያጠፉን ጌ ልማት እንመኜልን
ወኢንሻአኗሀ ኻሊቅኖም ይርደን
እስቲ ልሀንጅኔ መለስ ብልደን ጋሩን
የኢሀዲግ ዳዉላ ሊና የመኜዉን
በሀለፈዉ ዘመን ጭራሽ የቀራዉን
አርጎባን በስሙ መጥረሁን

በአርጎባ ስም ወረዳች መሀዊዱን

ጭራሽ የላዉ ጠፍደመል ያሊዉን

ሁሪያ እጌኛ ለድዩም

በነብሡ ቋንቋ ሆና ዉዥዠም

ድዩም ለነብሡ ሆነሎ ጌዉም

ሁድን ሁድንማ ሲሀንጅ በወገር

ይጌቤል ለጌታኖ ሹክር

በየንኖም ሃንጀን መኪና

በጌኖ ሄማ እቤጃና

ሲሀንጅማ የምራሁን የሀላፊዉን

ሀንዱን ሄማ መኻደሚ ሌፍ ሌፉን

ሀንደኛዉን ወሌ መኺደሚ ቴፍ ቴፉን

ኒቅደሚ እምበር በጌኖ ሩሽ ማለፉን

ላኪን በሀዋ ሩሽ እምበራ

ሌፍ ሌፉን የሚሄንጅ ጠያራ

ኤሌክትሪክም ገባ በጌኖ

ደመቃ አማሀራ ቤድኖ

እህዋዉ ሆና በቀጠር

ተአብ ሙሊ ቀራ መቼገር

መሯሯጥ የላዉ ለመድረስ

ሲልኩን መኻዶየል በኪስ

ሹምንም ሲያዋዢ ፊድ ለፊድ

መሡተር የላዉ ወሌ መፍሪድ

ሊና የሚበጁን እንሾሜልን

ሊና ያልሆናዉንም እንሽሬልን
መብቱ ቢንጅኖ ሆንዶልን
መልፊድ የላዉ መሯሯጥ
ሀኪም ፍለጋ ብልዶ ለምጣጥ
ይሜሄር ጀመራ ድዩም
ጅህልናም ሀላ ዉድም
ሁድ ሙሊ ኒእማ የናኝ
ድዩም በኢህአዴግ ኔ
የምልጠይቂ እምር ላኪን
ክልል የለናዉ ዞን
ሳናንስ ሀናስ ይሉነል
በማስ ስም ይጠርሁነል
ከም ከም ሲሉ የከፈነል
ከሜ ብልሆን ይሺለናል
ወረዳ መሆኒድ ሲችል
ብዙህ ወገንኖ ከሙን ቀርዶል
እነስ ሽእብ አርጎባ ነቀህ በል
ከመጠየቂድም ይቀራል
ከዉዥዣም ሁክም ይጌኘል
ዝም ቢሊ ጌ ይሀጢል
የቴኜሁም ነቀህ በሉ
የቴኛሡ ሀላ ሲሉ
በቴኜቦ ቀርዶል ሀሉ
ከም መሆኑን ወንቅዳህ